# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

# 6ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

በላይነሽ ደነቀ (ዶ.ር.)

ታሪኩ ነገሰ (ዶ.ር.)

**አርታኢዎች**

ትንሳኤ ጀምበሬ

ንጉሴ ዴአታ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምስል ገለፃ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


መቅድም .....iv

መግቢያ .....v

ምዕራፍ አንድ ባህላዊ ልብሶች ..... 1

ምዕራፍ ሁለት ዝነኛ አትሌቶች ..... 17

ምዕራፍ ሦስት ቃላዊ ግጥሞች ..... 31

ምዕራፍ አራት ዘመናዊ ግብርና ..... 44

ምዕራፍ ስድስት ፀረ አደንዛዥ ንጥረ ነገሮች ..... 67

ምዕራፍ ሰባት የጥላቻ ንግግር ..... 81

ምዕራፍ ስምንት ኤችአይቪ/ኤድስ ..... 96

ምዕራፍ ዘጠኝ ልማዳዊ ተግባራት ..... 109

ምዕራፍ አሥር ሴቶችን ማብቃት ..... 124

ሙዳየቃላት ..... 139

# መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር “ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለው ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ” በሚል ትኩረት ሰጥቶ አዲስ ሥርዓተትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህም መሠረት ቀድሞ በነበረው ሥርዓተትምህርት ላይ ታይቶ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምር ተደርጓል። ከምርምሩ የተገኙ አቅጣጫዎችም የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው። ስለሆነም ስርዓተትምህርቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ፣ እና በተግባራዊ መማር ላይ የተመሠረተ የመማር ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ተቀርጿል።

ሥርዓተትምህርቱን መሠረት በማድረግም የትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ በመሆኑ ይህ አማርኛን እንደአፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሊዘጋጅ ችሏል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency)፣ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ እንዲሁም ተግባቦታዊ የመማር ዘዴን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ አንፃር መጽሐፉ በቀድሞው የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል።

# መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች አሉት። እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በሥሩ ስድስት ንዑሳን ትምህርቶችን አካቷል። እነዚህም ትምህርት አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ሁለት መናገር፣ ትምህርት ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት አራት መጻፍ፣ ትምህርት አምስት ቃላት እና ትምህርት ስድስት ሰዋስው ናቸው። እያንዳንዱ ትምህርት በመርሃ-ትምህርቱ በተደለደለው መሠረት በክፍለጊዜ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በሥሩ መመሪያዎችን፣ ትዕዛዛትን፣ መልመጃዎችን እና ተግባራትን አካቷል። ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመ ተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረ ተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ነው። የቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ዘዴን ተከትለዋል። ከዚህ አንጻር የመማሪያ መጽሐፉ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ተደርጓል።

# ምዕራፍ አንድ

# ባህላዊ ልብሶች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ዓረፍተነገር ለመመሥረት የሚያስችሉ የቃላት አፃፃፍ ህጎችን አዳምጣችሁ ትገልጻላችሁ፤
- አቀላጥፎ ማንበብን ትለማመዳላችሁ፤
- በዓረፍተነገር ውስጥ ላሉ ውስብስብ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፤
- ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀ ፅሑፍ ውስጥ የሚገኝ ፍቺን ለመረዳት ተገቢ ንበትንና ስርዓተ ነጥቦችን ትጠቀማላችሁ፤
- ቃላትን እየነጠላችሁ ታነባላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**ክፍለጊዜ አንድ**

በዚህ ትምህርት "የሀገራችን የሽመና ጥበብ አጀማመር" በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች በትኩረት ትሠራላችሁ::

# የሀገራችን የሽመና ጥበብ አጀማመር



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ስለሽመና የምታውቁትን ተናገሩ።
2. ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።
3. ርዕሱን መነሻ በማድረግ የምንባቡን መልዕክት ተናገሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የሽመና ሥራ እንዴት ተጀመረ?
2. ለሽመና ሥራ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች ምንምን ናቸው?

## ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በቃል አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

**ምሳሌ**

**አቤቱታ፡** ለበላይ አካል የሚቀርብ የማህበረሰቡ ቅሬታ ሆኖ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርብ የሚችል ጥያቄ፣ ማመልከቻ ወይም ይግባኝ

1. የትውልድ ቀዬ
2. የዕለት ምግብ
3. እየገነነ
4. ዘመን አመጣሽ

## ክፍለጊዜ ሦስት

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ለሽመና ሥራ መስፋፋት አስተዋጽዖ ያደረጉ ማኅበረሰቦች እነማን ናቸው?
2. ለሽመና ሥራ የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?
3. የሸማ ሥራ ተፈላጊነት እየገነነ የመጣበት ምክንያት ምን እንደሆነ ግለጹ።
4. በማዳመጥ ጊዜ የያዛችኋቸውን ቃላት ከዘረዘራችሁ በኋላ አውዳዊ ፍቺያቸውን ለጓደኞቻችሁ አብራሩ።
5. ያዳመጣችሁትን ጽሑፍ ጭብጥ ባጭሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት አያያዥ ቃላትን ተጠቅማችሁ ንግግር ለማድረግ የሚያስችላችሁ ተግባር ቀርቦላችኋል። በመሆኑም ትዕዛዙን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ተግባር ሥሩ።

**ተግባር አንድ**

ስለባህላዊ ልብሶች መስፋፋትና ጠቀሜታ ምክንያት እያቀረባችሁ በቡድን ተወያዩ። በጋራ የተስማማችሁበትን ሀሳብ በቡድን ተወካዮቻችሁ አማካይነት በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ። በንግግራችሁ ውስጥም በዚህም ምክንያት፣ ስለዚህ፣ ስለሆነ፣ እና የመሳሰሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቀሙ፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ቀጥሎ "የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብሶች" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሯቸው። ምንባቡን ስታነቡ ሀሳቡን መረዳታችሁን ለማረጋገጥ ራሳችሁን ጥያቄ በመጠየቅና ሀሳቦችን ርስበርስ በማስተሳሰር በለሆሳስ አንብቡ።



## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ በቃልመልሱ።**

1. "ህብረቀለማት፣ እሴት፣ ሸንቃጣ፣ እና ልጃገረድ" ለሚሉት ቃላት ፍቺ ስጡ።
2. ባህላዊ ልብሶች ማለት ምን ማለት ነው?
3. ስዕሉን በመመልከት የተገነዘባችሁትን ተናገሩ።

# የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብሶች

አንድ ማኅበረሰብ ማንነቱን ከሚገልጽበትና እሴቱን ከትውልድ ወደትውልድ ከሚያስተላለፍበት መንገዶች አንዱ ባህላዊ ልብሱ ነው። ኦሮሞ እንደህዝቡ ብዛትና እንደመሬቱ ቆዳ ስፋት ሁሉ ባህላዊ ልብሶቹም በርካታ ናቸው። ካሉት ባህላዊ ልብሶች አንዱ የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብስ ነው። በወሎ ኦሮሞ ዘንድ ለተለያዩ ባህላዊ ጉዳዮች የሚውሉ ልዩልዩ ባህላዊ ልብሶች አሉ። **ከነዚህም** ውስጥ ለተለያዩ ጉዳዮች ወንዶችና ሴቶች የሚለብሷቸውን ማንሳት ይቻላል።

የወሎ ልጃገረዶች ከሚለብሱት ባህላዊ ልብሶች መካከል አንዱ ቶርቢ ይባላል። ቶርቢ ብዙውን ጊዜ ከፍየል ቆዳ የሚሠራ ነጭ ቀበቶ ሆኖ ልጃገረዶች ወገባቸው ላይ እንደመቀነት የሚታጠቁት ነው። እንደወሎ ኦሮሞ ባህል አንዲት ልጃገረድ ቶርቢ የምትታጠቀው ድንግል (ቀሬ) መሆኗን ለማሳየት ነው። እንዲሁም ፍቅረኛ እንዳላት ለማሳወቅም ጭምር ነው። አልፎ አልፎ እጮኛ

እንዳላት ለመግለጽም የምትታጠቅበት ጊዜ አለ። በሌላም መልኩ ልጃገረዶች ቶርቢ የሚታጠቁት ወገባቸው ሸንቃጣ እንዲሆንና ውበታቸው እንዲጨምር ነው። ባጠቃላይ ቶርቢ የወሎ ኦሮሞ ልጃገረዶች ድንግልናና ፍቅረኛ እንዳላቸው ለማመልከት ወገባቸው ላይ የሚታጠቁት ነው።

የወሎ ኦሮሞ ሴቶች የሚለብሷቸው ሌሎች የባህል ልብሶችም አሏቸው። ከነዚህም መካከል ዱንጉሳ፣ ሶርዲያ፣ ሰበታ (መቀነት)፣ ጎንዶቤ፣ እና የመሳሰሉትን መዘርዘር ይቻላል። ዱንጉሳ የታጩ ልጃገረዶች ብቻ የሚለብሱት ነው። ይህንን የለበሰች ልጃገረድ ወንዶች ለእጮኛነትም ሆነ ለፍቅረኛነት አይጠይቋትም። ሶርዲያና ሰበታ ደግሞ ያገቡ ሴቶች የሚታጠቁት ነው።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች የተረዳችሁትን ፍሬ ነገር ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ካነበባችኋቸው አንቀጾች በመነሳት ቀጥሎ የሚመጣውን ሐሳብ ገምቱ፡፡

በወሎ ኦሮሞ ዘንድ ወንዶችም የተለየ የአለባበስ ሥርዓት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ጸጉራቸው ላይ የሚሰኩት ማበጠሪያ (ጌጥ) አንዱ ነው፡፡ ማበጠሪያ ከእንጨትም ከብረትም የሚሠራ ሆኖ ወጣቶች ፍቅረኛቸውን ለመምረጥ ይጠቀሙበታል። በተጨማሪም ለውበት መገለጫነትም ይውላል። ሂንቴ ወጣቶች በጸጉራቸው ሥር

የሚጠመጥሙት ሲሆን ባሩዲ እና ጋርፎዬ ደግሞ በአንገታቸው ላይ የሚያጠልቁት ነው። ባሩዲ ከጥይት ቀለሃ በባለሙያ ተቀርጾ የሚዘጋጅ የፍቅር ቃል ኪዳንን ለማሳየት የሚውል ነው። ጋርፎዬ በተለያዩ ህብረቀለማት ባሸበረቁ ትናንሽ ጨሌዎች በክር በማያያዝ አንገት ላይ ይደረጋል።

ወንዶች ወገባቸው ላይ የሚታጠቁት ጌጥ ደግሞ ጎጆባ ይባላል። ጎጆባን ለውበት ብቻ ሳይሆን ጀግንነትንም ለመግለጽ ይጠቀሙበታል። ይህም በወሎ ኦሮሞ ዘንድ የጀግንነት ምልክት ተደርጎ ይታያል። መስነፋ የሚባለው ልብስ ደግሞ ከጥጥ የሚሠራ ሆኖ ወንዶች ከወገባቸው በታች የሚለብሱት ነው። መስነፋን የሚለብሱት ወጣቶችና ትላልቅ ሰዎች ብቻ ናቸው። ህጻናት መስነፋ እንዲለብሱ በባህሉ አይፈቀድም።

ባጠቃላይ የወሎ ኦሮሞ ማኅበረሰብ እንደማንኛውም ማኅበረሰብ በአለባበሱ ባህሉንና ማንነቱን ሲገልጽበት ኖሯል፤ አሁንም እየገለጸበት ይገኛል። ባህላዊ ልብሶቹን ሥርዓተጸታን፣ ዕድሜን፣ እና የሥራ ድርሻን ለመለየት ይጠቀሙበታል። በዚሁ መሠረት ኅብረተሰቡ ባህሉን፣ እሴቱን እና ሰፉውን (ግብረገብ) ከትውልድ ወደትውልድ ያስተላልፍበታል።

(ከ6ኛ ክፍል አፋን ኦሮሞ የተማሪ መጽሓፍ ላይ ተተርጉሞና ተሻሽሎ የተወሰደ)

ክፍለጊዜ ስድስት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።**

1. ባህላዊ ልብስ ለአንድ ማኅበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳ ምንድን ነው?
2. ቀርቢ ከምን እንደሚሠራና ለምን አገልግሎት እንደሚውል ግለጹ።
3. የወሎ አሮሞ ሴቶችና ልጃገረዶች የሚለብሷቸውን ባህላዊ ልብሶች ዘርዝራችሁ አገልግሎታቸውን አብራሩ።
4. የወሎ አሮሞ ወንዶች የሚለብሷቸውን ባህላዊ ልብሶች ዘርዝራችሁ አገልግሎታቸውን አብራሩ።
5. በወሎ ኦሮሞ ያገባችና ያላገባች ሴትን እንዴት መለየት ይቻላል?
6. ህጻናት እንዳይለብሱ በባህሉ የማይፈቀድላቸው የልብስ ዓይነት የትኛው ነው?
7. በአንቀጽ አንድ "ከነዚህም..." የሚለው አያያዥ ቃል ምንን ያመለክታል?
8. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

**ለምሳሌ፡ ቀለሃ፡ ጥይት ከተተኮሰ በኋላ የሚቀር የባሩድ መያዣ ባዶ ቀፎ ብረት**

1. የቆዳ ስፋት
2. መገለጫ
3. ማበጠሪያ
4. ሥርዓተጾታ
5. ያሸበረቀ
6. ሰፉ (ግብረገብ)

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## አቀላጥፎ ማንበብ

**ተግባር ሁለት**

1. በጥንድ በጥንድ በመሆን "የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብሶች" የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሁለት አንቀጾች ሥርዓተነጥቦችንና የሐረግ አከፋፈልን ተከትላችሁ ተራበተራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

2. "የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብሶች" የሚለውን ምንባብ ከሁለተኛው አንቀጽ ጀምሮ ተራ በተራ አንድ አንድ አንቀጽ ድምጽ በማሰማት በአንድ ደቂቃ ውስጥ በፍጥነት አንብቡ።

**ክፍለጊዜ አስር**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

የዚህ ትምህርት ትኩረት ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀም እና መነሻ ሀሳቦችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መጻፍ ነው። ሥርዓተነጥቦችን ለመረዳት የሚያስችላችሁ ማስታወሻም ቀርቦላችኋል። በመሆኑም ቀጥሎ የቀረቡላችሁን የመልመጃ ጥያቄዎች በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሠረት ሥሯቸው።

### ሥርዓተነጥቦች

1. ነጠላ ሠረዝ (፣)

   ይህ ምልክት በዓረፍተነገር ውስጥ የሚዘረዘሩ ነገሮችን፣ ስሞችን፣ ሀረጎችን፣ ወዘተ. ለመለየት ያገለግላል፡፡

   ለምሳሌ፡ ፍራፍሬ የሚባሉት ሎሚ፣ ብርቱካን፣ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2. አራት ነጥብ(፡፡)

   በዓረፍተነገር መጨረሻ እየገባ ዓረፍተነገሩ መጠናቀቁን ያመለክታል፡፡

   ለምሳሌ፡ ሐዋ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡

3. የጥያቄ ምልክት (?)

   መልስ የሚፈልጉ ዓረፍተነገሮች መጨረሻ ላይ ይገባል፡፡

   ለምሳሌ፡ ፍራያል ለምን ትምህርት ቤት ቀረ?

**መልመጃ ሦስት**

## ክፍለጊዜ አስራአንድ

**ሀ. ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ በማስገባት ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ።**

ለምሳሌ፡

ባህላዊ ልብሶች ከሚባሉት መካከል ጋቢ ኩታ በርኖስ ጥበብ ካባ ሊጠቀሱ ይችላሉ

መልስ፡ ባህላዊ ልብሶች ከሚባሉት መካከል ጋቢ፣ ኩታ፣ በርኖስ፣ ጥበብ፣ እና ካባ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

1. ባህላዊ ልብሶቻችን ዓለማቀፋዊ ተወዳጅነት አግኝተዋል ተፈላጊነታቸውም ጨምሯል
2. ታዳሚዎች ከመቀመጫቸው ተነስተዋል ጭብጨባው ደምቋል ሙሽሮቹ ወደዳሱ ሳይገቡ አልቀረም
3. ባህላዊ ልብሶች መቼ መቼ ይለበሳሉ
4. ባህላዊ ልብሶች ከጥጥ ከበግ ፀጉር ከተልባ እግርና ከቆዳ ይሠራሉ
5. በችኮላ የተሠራ ሥራ ሁሉ ስህተት አያጣውም
6. ለምን አረፈድክ

## ክፍለጊዜ አስራሁለት

**ለ. የሚከተሉትን ሥርዓተነጥቦች በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።**

(፣) (?) (።)

**ሐ. የሚከተሉትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ዓረፍተነገር ጻፉ።**

- የተሰማኝ ደስታ
- የለበስኩት ልብስ

- የተዋወቅኳቸውልጆች
- የገዛሁት ደብተር

**ክፍለጊዜ አስራሦስት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ቀጥሎ የተለያዩ ቃላትን እንድትጠቀሙ የሚያስችላችሁ መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዞቻቸው መሠረት በትኩረት ሥሩ።

### መልመጃ አራት

**ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በትክክለኛ ቦታቸው በማስገባት ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀለም | ውበት | ሽማ | ባህላዊ |
| ቀልብ | ህብር | ቁጥር | አሻራ |


**ምሳሌ፡** በዓውደ ዓመት ጊዜ ብዙዎቻችን ባህላዊ ልብስ መልበስ እንወዳለን።

1. ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች የሚዘጋጁት ባህላዊ ልብሶች የየባህሉ ________ አርፎባቸዋል።
2. ብሔር ብሔረሰቦች የተለያየ ______ ያላቸው የባህል ልብሶች አሏቸው።
3. ባህላዊ ልብሶቻችን ከተፈጥሮ ጥጥ ስለሚዘጋጁ ምቾትና ________ አላቸው።
4. ባህላዊ ልብሶቻችን ከጥልፎችና ከጥበቦች ጋር ________ ፈጥረው ________ ይስባሉ።

5. ባህላዊልብሶቻችንን ገዝተው የሚለብሱት የውጪ ሀገር ዜጎች ________ ቀላል አይደሉም።

## ክፍለጊዜ አስራአራት

ለ. ባህላዊና ዘመናዊ የሆኑ ልብሶችን ለይታችሁ በሚከተለው የቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ ጻፉ።





ሐ. በቢጋሩ ተዋረድ መሠረት በተዘረዘሩት ቃላት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡ ጋቢ ከጥጥ የሚሠራ ባህላዊ ልብስ ነው።

## ክፍለጊዜ አስራአምስት

መ. ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በተገቢ ቃላት አሟልታችሁ ጻፉ።

1.




2.




**ክፍለጊዜ አስራስድስት**

**ሠ. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ የርባታ ምዕላድ የወሰዱትን ቃላት ለዩ።**

ምሳሌ፡- "ልብሶች" የሚለው ቃል /-ኦች/ የሚል ተዘውታሪ ምዕላድ ወስዷል።

1. ቤቶች
2. መኪናዎች
3. በጊቱ
4. ገዳማት
5. አበባዎች
6. ሀረጋት
7. መምህራን
8. ልብሳችን
9. ተማሪዎቹ
10. ደብተሬ

**ክፍለ ጊዜ አስራሰባት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት የወልና የተጸውዖ ስሞች በዓረፍተነገር ውስጥ እንድትጠቀሙ የሚረዳችሁ ማስታወሻና መልመጃ ቀርቧል።

በመሆኑም ቀጥሎ የቀረበላችሁን የመልመጃ ጥያቄዎች በተሰጧችሁ ትዕዛዞች መሠረት በትኩረት ትሠራላችሁ።

**ማስታወሻ**

የወል ስም በተፈጥሮ አንድ ዓይነት የሆኑ ነገሮች በጠቅላላው የሚጠሩበት የጋራ ስም ነው፡፡ የወል ስሞች የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን (ምዕላዶችን) ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ወንድ፣ ሴት

የተጸውዖ ስም ደግሞ አንድ ሰው ወይም ነገር የሚጠራበት የግል ስም የያዘ ነው፡፡ እንዲሁም የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን የማይወስዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ፋጡማ፣ አምቦ፣

**መልመጃ አምስት**

ሀ. የሚከተሉትን ስሞች በተጸውዖና በወል ስሞች ለይታችሁ አመልክቱ።

| | | |
|---|---|---|
| ሰው | ጅማ | ዱከም |
| መጽሐፍ | አልማዝ | ጣና |
| ተራራ | ምግብ | ልብስ |
| እህል | ለሊሴ | መኪና |

| ተጸውዖ ስሞች | የወል ስሞች |
|---|---|
| • ለሊሴ<br>•<br>•<br>• | • መኪና<br>•<br>•<br>• |

ለ. ከላይ በተዘረዘሩትየተጸውዖና የወል ስሞች ተጠቅማችሁ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

**ክፍለጊዜ አስራስምንት**

ሐ. እናንተም የምታውቋቸውን የወል እና የተጸውዖ ስሞች በደብተራችሁ ላይ ጽፋችሁ ዘርዝሩ።

መ. የሚከተሉትን ውስብስብ ቃላትና ሐረጋት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| 1 እንደ-ለበስ-ኡ | እንደለበሱ |
| 2 ፍላጎት-ኡ-ን | ፍላጎቱን |
| 3 ቀለበት-ኦች | ቀለበቶች |
| 4 ሽማግሌ-ዎች-ኡ | ሽማግሌዎቹ |
| 5 ከ-መስተንግዶ-ው | ከመስተንግዶው |
| 6 የ-ብዙ-ዎች-ኣችን | የብዙዎቻችን |
| 7 በ-ጥበብ-ኧኛ-ዎች-ኡ | በጥበበኛዎቹ |
| 8 ልብስ-ኦች-ኣችን-ን | ልብሶቻችንን |

# ምዕራፍ ሁለት

## ዝነኛ አትሌቶች

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ቃላትን ከምዕላዶች ትለያላችሁ፤
- ምዕላዶችን በማጣመር ቃላት ትመሠርታላችሁ፤
- የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ትናገራላችሁ፤
- በክፍል ደረጃው የቀረበ ምንባብ ፍቿን ለመረዳት ድምፀትን በስርዓተ ነጥቦች ደረጃ ትጠቀማላችሁ፤
- አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- ጥቅል ስሞችንና ተውሳከግሶችን ትለያላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት "ብርቅዬዋ አትሌት" በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ አዳምጣችሁ የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# ብርቅዬዋ አትሌት




## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በፎቶው ላይ የምትመለከቷት አትሌት ማን ትባላለች? በየትኛው የአትሌቲክስ ዘርፍ ትሳተፋለች?
2. አትሌት የሚባሉት በየትኛው ስፖርት አይነት የሚሳተፉ ናቸው?
3. ከዚህ በፊት ስለታዋቂ አትሌቶች የሕይወት ታሪክ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ካወቃችሁ የማንን? የሕይወት ታሪኳን/ታሪኩን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አትሌት መሠረት ኑሮን ለማሸነፍ ምን ምን ተግባራትን አከናውናለች?
2. የአትሌት መሠረት ተሰጥዖ ጎልቶ የወጣው መቼ ነው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ክፍለጊዜ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. አትሌት መሠረት የመጀመሪያ ዓለምአቀፍ ውድድሯን ለማድረግ የሄደችው የት ነበር?
2. አትሌት መሠረት ፈጣን ሰዓት (ሪኮርድ) ያስመዘገበችው የት የት ነበር?
3. አትሌት መሠረት የሀገሯ ሰንደቅዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረገችው እንዴት ነው?
4. ከአትሌት መሠረት ታሪክ ምን ተማራችሁ?
5. በትምህርት ቤቶችና በአትሌቲክስ መካከል ምን ዓይነት ዝምድና ያለ ይመስላችኋል?

**ክፍለጊዜ ሦስት**

**ለ. ለተሠመረባቸው ቃላት በቃል አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

**ምሳሌ፡** አትሌት መሠረት **ተስፋዋን** ለማሳካት ከቀድሞው በበለጠ ልምምዷን ማጠናከር ጀመረች።

**ተስፋ፡** ባላት ብቃት ወደፊት ውጤታማ እንደምትሆን መገመት

1. በዕድሜም ሆነ በአካል እያደገች ስትመጣ በግንባታ ሥራ ውስጥ **ተቀጥራ** ሠርታለች።
2. በ1999 ዓ.ም. በጀርመን ስቱትጋርት በ3 ሺህ ሜትር የቤት ውስጥ ውድድር **ሪኮርድ** አስመዘገባለች።

3. አትሌት መሠረት የሀገሯ ሰንደቅዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረገች ብርቅዬ አትሌት ናት።
4. በአሜሪካ ካሊፎርኒያ የሁለት ማይል ሩጫ ውድድር ተካፍላ ሪኮርድ አስመዝግባለች።

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችሉ ሀሳቦች ቀርቦላችኋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ንግግር ታደርጋላችሁ።

**ተግባር አንድ**

1. "ብርቅዬዋ አትሌት" ከሚለው የሕይወት ታሪክ የተገነዘባችሁትን ቁምነገር በቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁባቸውን ነጥቦች በተወካዮቻችሁ አማካይነት በንግግር አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

2. እናንተም ስለምታውቋቸው ሌሎች ታዋቂ አትሌቶች የሕይወት ታሪክ ሰው በመጠየቅ ወይም መጽሐፍ በማንበብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ቀጥሎ “ፋናወጊዋ አትሌት” በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቻቸው መሠረት ሥሩ። ምንባቡን ስታነቡ ከአንደኛው አንቀጽ ጀምራችሁ በየአንቀጾቹ መጨረሻ ቆም እያላችሁና የአንቀጾችን መልዕክት እያጠቃለላችሁ አንብቡ። ያልተረዳችሁት አንቀጽ ሲኖር በድጋሜ በማንበብ ለመገንዘብ ሞክሩ።

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ርዕሱን መነሻ በማድረግ የምታውቋቸውን ፋናወጊ አትሌቶች ዘርዝሩ።
2. ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ቀዳማዊት እመቤት　　　　ሐ. ርዕሰብሔር

   ለ. ፋናወጊ

## ፋናወጊዋ አትሌት

ኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ በኦሮሚያ ክልል በበቆጂ ከተማ በ1964 ዓ.ም. ተወለደች። አስተዳደጓም ከብት እያገደች፣ እህል እየፈጨችና ሌሎች ሥራዎችን እየሠራች ቤተሰቦቿን በማገዝ ነበር። ደራርቱ ትምህርት ቤት የገባችውም ከጓደኞቿ ሁለት ዓመት ዘግይታ ነበር። ትምህርት ቤት በሰዓቱ ለመገኘት ስትል ሩጫን የዕለት ተዕለት ተግባሯ አደረገችው። የሯጭነት ምሥጢሯ

መገለጥ የጀመረውም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቷ ውስጥ ነበር። በወቅቱ የስፖርት መምህሯ ባዘጋጁት የ400 ሜትር የአጭር ርቀት ሩጫ ላይ አሸነፈች። ይህም ለወደፊቱ ድል የሚወልድ ብቃት ለመቋጠር አስቻላት። በዚያ ዘመን መሮጥ ለሴት ልጆች አስቸጋሪ ነበር። የደራርቱ እግሮች ግን የጎጂ ልማድ ተፅዕኖዎችን ሰብረው መውጣት ጀመሩ። ትምህርት ቤቷን እየወከለች በ800 እና በ1500 ሜትር ርቀቶች ተወዳድራ በተደጋጋሚ አሸንፋለች።

ያገኘቻቸው ድሎችም ወደሀገር አቀፍ ውድድሮች ለመምጣት ምክንያት ሆናት። በ17 ዓመቷ በሀገር አቋራጭ ሩጫ ላይ አሸናፊ ሆነች። ማሸነፏን ተከትሎ በ1980 ዓ.ም. ለማረሚያ ቤቶች ስፖርት ክለብ ፈረመች። ከዚያም በ1981 ዓ.ም በኖርዌይ ስታቫንገር ከተማ በስድስት ኪሎ ሜትር የመጀመሪያዋ የሆነውን ዓለም አቀፋዊ ውድድር 23ኛ ወጣች። በውጤቱ እሷም ሆነች አሰልጣኟ ተስፋ ሳይቆርጡ በቂ ዝግጅት አደረጉ። በዓመቱ ፈረንሳይ ውስጥ በተደረገ ውድድር ይህንኑ ርቀት በወርቅ ሜዳልያ አካካሰችው። በዚያው ዓመት ቡልጋሪያ ላይ በተካሄደው የ10 ሺህ ሜትር ውድድር አሁንም አንደኛ ወጣች። በኦሎምፒክ ወድድሮችም እንድትሳተፍ ተመረጠች። በመሆኑም በ1984 ዓ.ም. በባርሴሎና ተዘጋጅቶ በነበረው ኦሎምፒክ በ10 ሺህ ሜትር ተወዳደረች። ደራርቱ የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት የወርቅ ሜዳልያ ተሸላሚ በመሆንም አጠናቀቀች።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅ ሜዳልያ ያገኘችው የት ነው?
2. ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ እስካሁን ከነበባችሁት አንቀጾችና ቀጥሎ ከምታነቡት አንቀጽ መረጃዎችን በመፈለግ አሟሉ።

| የውድድሩ ርቀት | ያሸነፈችበት ሀገር | ያሸነፈችበት ዓመት ምህረት | ያገኘችው ሽልማት |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

በዚህም እስካሁን ድረስ በብዙዎች ዘንድ የአፍሪካ የስፖርቱ ዓለም ቀዳማዊት እመቤት እንደሆነች ትቆጠራለች። ይህን ድል አስመዝግባ ወደሀገሯ እንደተመለሰች በርዕሰብሔሩ አማካይነት የሻለቃነት ማዕረግ ተሰጥቷታል። ከዚያም በኋላ በሀገርአቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ሜዳልያዎችን አግኝታለች። ከዓመታት በኋላ በ1993 ዓ.ም. በአውስትራሊያ ዋና ከተማ በሲድኒ በተደረገው የኦሎምፒክ ውድድር ላይ ተሳተፈች። በውድድሩ በ10 ሺህ ሜትር ርቀት የወርቅ ሜዳልያ ተሸላሚ ሆነች። በማሸነፏም በኦሎምፒክ ውድድሮች በ10 ሺህ ሜትር ርቀት ሁለት ጊዜ የወርቅ ሜዳልያ ያገኘች የመጀመሪያዋ ሴት አትሌት ሆነች። አትሌቷ በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ የበርካታ አትሌቶችን የድል

መንገድ ጠርጋለች። በመሆኑም ፋናወጊዋ አትሌት በኢትዮጵያውያንም ሆነ በመላው አፍሪካውያን ልብ ውስጥ ነግሳለች። ኮሎኔል አትሌት ደራርቱ በአሁኑ ጊዜ ተተኪዎችን ለማፍራት ልምዷን እያካፈለች ትገኛለች።

(ሰለሞንና ስምረት። 2000። ደማቆቹ። ገጽ 317-330 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።**

1. ኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ "ፋናወጊዋ አትሌት" የተባለችው ለምንድን ነው?
2. ኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ በልጅነቷ ቤተሰቦቿን ምን ምን በመሥራት ትረዳ ነበር?
3. የኮሎኔል አትሌት ደራርቱ የሯጭነት ምስጢር የተገለጠው መቼ ነው?
4. እንደኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ ከትምህርት ቤት ስትመለሱ ቤተሰቦቻችሁን ምንምን በመሥራት እንደምታግዙ በዝርዝር ጻፉ።
5. የምንባቡን ዋና መልዕክት በአጭሩ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በተገቢ ቃላት አሟሉ።

1. ኮሎኔል አትሌት ደራርቱ በሲድኒ በተደረገው የኦሎምፒክ ውድድር ላይ የተሳተፈችው በ _______ ዓ.ም ነው።
2. ኮሎኔል አትሌት ደራርቱ የመጀመሪያዋ የሆነውን ዓለም አቀፍ ውድድር ተሳትፋ 23ኛ የወጣችው በ _______ ኪሎ ሜትር ነው።
3. የኮሎኔል አትሌት ደራርቱ የትውልድ ቦታ _______ይባላል።
4. ለኮሎኔል አትሌት ደራርቱ የሻለቃነት ማዕረግ የተሰጣት በ_______ ነው።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

# አቀላጥፎ ማንበብ

**ተግባር ሁለት**

1. "ፋናወጊዋ አትሌት" የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያውን አንድ አንቀጽ ሁለት ሁለት እየሆናችሁ ተራበተራ ድምፅ በማሰማት በፍጥነትና በትክክል አንብቡ።

## ክፍለጊዜ አስር

2. "ፋናወጊዋ አትሌት" የሚለውን ምንባብ ሥርዓተነጥቦችን ጠብቃችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ በትክክል አንብቡ።

ክፍለጊዜ አስራአንድ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

የዚህ ትምህርት ትኩረት አጫጭር አንቀጾችን መጻፍ ነው። በመሆኑም ቀጥሎ የቀረቡትን ተግባራት በትዕዛዞቻቸው መሠረት ሥሯቸው።

**ተግባር ሦስት**

1. ሰዎች ንጽህናን ለመጠበቅ የት እንደሚሄዱና ምን እንደሚያደርጉ የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

ክፍለጊዜ አስራሁለት

2. እንደኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ በአትሌቲክስ ወይም በሌሎች መስኮች ውጤታማ ለመሆን ምንምን እንደምታደርጉ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ክፍለጊዜ አስራሦስት

3. ከኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ የህይወት ታሪክ የተማራችሁትን ቁምነገር በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

ክፍለጊዜ አስራአራት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ተመሳሳይ ቃላትን የምትለዩበት መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት በትኩረት ሥሩ።

**መልመጃ ሦስት**

**ከተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ በፍቺ ተያያዥ የሆኑትን ለይታችሁ በየምድባቸው አስቀምጡ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| መርዳት | ማገድ | ማካፈል | ማገዝ |
| ማጋራት | በርካታ | ብዙ | መጠበቅ |
| መተባበር | መከልከል | አያሌ | |

| ቃል | በፍቺ ተያያዥ |
|---|---|
| ለምሳሌ፡ መርዳት | ማገዝ፣ መተባበር |
| ማካፈል | |
| በርካታ | |
| መጠበቅ | |

**ክፍለጊዜ አስራአምስት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት የጥቅል ስሞችንና ምዕላዶችን ከቃላት እንድትለዩ የሚረዳችሁ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። እንዲሁም ምዕላዶችን በማጣመር ቃላት እንድትመሠርቱ፣ የጊዜ ተውሳከግሶችን በዓረፍተነገር ውስጥ እንድትጠቀሙ የሚያግዛችሁ መልመጃዎች ቀርበዋል። ስለሆነም ጥያቄዎቹን በተሰጧችሁ ትዕዛዞች መሠረት ሥሯቸው።

## ተግባር አራት

ተማሪዎች ንፅህና መጠበቅን በተመለከተ በምልክት የተገለጸን ድርጊት ይገምታሉ፡፡ የገመቱትን ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት ከፋፍለው ዓረፍተነገር ይመሠርታሉ፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ተማሪ እጅ መታጠብን በምልክት ያሳያል፡፡ ሌሎች ደግሞ ድርጊቱን ለምሳሌ “አበበ ትናንት እጁን ታጠበ” ብለው በዓረፍተነገር ቢገልጹ የተገለጸው ዓረፍተነገር ከጊዜ አንጻር ኃላፊ ጊዜ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚገለጸውን ድርጊት የሚከተሉትን የጊዜ አመልካቾች በመጠቀም ዓረፍተነገር በመመሥረት ግለጹ።

1. ትናንት
2. አሁን
3. ወደፊት
4. ዛሬ
5. ነገ

**ክፍለጊዜ አስራስድስት**

## ሀ. ምዕላዶችን ከቃላት መለየት

### መልመጃ አራት

**ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ቅጥያ ምዕላዶቻቸውን ለዩ።**

**ለምሳሌ፡**

| | ቃላት | ምዕላዶች |
|---|---|---|
| 1 | ቤቶች | ቤት-ኦች |
| 2 | ብልጠት | ብልጥ-ኧት |
| 3 | ቃላት | ቃል-ኣት |

1. ሰውነት
2. ምላሰኛ
3. ልጆች
4. መምህራን
5. ቀልደኛ
6. ግንበኛ
7. ልጅነት
8. ቤተኛ

**ክፍለጊዜ አስራሰባት**

**ለ. ምዕላዶችን በማጣመር ቃላት መመስረት**

**መልመጃ አምስት**

**የሚከተሉትን ምዕላዶች በማጣመር ቃላት መሥርቱ።**

| | መነጣጠል | ማጣመር |
|---|---|---|
| 1 | ሰንደቅ-ዓላማ-ኣችን | ሰንደቅዓላማችን |
| 2 | የ-ስኬት-አማ-ነት-ኣቸው | ________ |
| 3 | ተ-ወዳጅ-ነት-ን-ም | ________ |
| 4 | አትሌት-ኦች-ኣችን | ________ |
| 5 | ሊ-ያጋጥም-ኡ-ኣቸው | ________ |
| 6 | የ-ብዙ-ዎች-ኣችን | ________ |
| 7 | ተተኪ-ዎች-ን | ________ |
| 8 | መንገድ-ኧኛ | ________ |
| 9 | ቤት-ኧ-ሰብ-ኦች-ኣችን | ________ |
| 10 | ተማር-ኢ-ዎች-ኡ | ________ |

**ክፍለጊዜ አስራስምንት**

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ስሞች የጥቅል ስሞችን ለይታችሁ አውጡ::**

እህል     አዳማ     ጳጉር

ወንጪ     ኤቢሲ

**ለ. በሠንጠረዥ ውስጥ ለቀረቡት ጥቅል ስሞች በሥራቸው የሚጠቃለሉትን ስሞች ጻፉ።**

| ጥራጥሬ | ቤት | ፍራፍሬ | የዱር እንስሳት |
|---|---|---|---|
| ለምሳሌ፡ አተር | | | |
| ባቄላ | | | |
| ሽምብራ | | | |
| አኩሪ አተር | | | |

## የጥቅል ስም

**ማስታወሻ**

ጥቅል ስም ነገሮች በአንድነት ተጠቃለው በአንድ ቦታ ላይ ሲገኙ በጅምላ የሚጠሩበት ስም ነው፡፡ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን (ምዕላዶችን) አይወስዱም፡፡ በዚህም ከወል ስም ይለያሉ፡፡ ለምሳሌ ጥራጥሬ

# ምዕራፍ ሦስት

## ቃላዊ ግጥሞች

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- አዲስ የተማራችኋቸውን ቃላት አዳምጣችሁ ጥቅም ላይ ታውላላችሁ፤
- ግጥምን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፤
- ግጥም ትጽፋላችሁ፤
- በዓረፍተነገሮች ውስጥ ቅንፍንና ህዝባርን ትጠቀማላችሁ፤
- የተማራችኋቸውን አዳዲስ ቃላት ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ በምታነቧቸው ቃላዊ ግጥሞች ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- የጊዜ ተውሳከግሶችን ትለያላችሁ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ።

ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ስለቃላዊ ግጥሞች ምንነትና ጠቀሜታ የምትረዱበት ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ቀጥሎም “የአጨዳ ጊዜ” በሚል ርዕስ የቀረበ ቃላዊ ግጥም ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረት የቀረበውን መልመጃ ትሠራላችሁ።

## ማስታወሻ

ቃላዊ ግጥሞች መልዕክትን በቃል የሚያስተላልፉ የማህበረሰብ ፈጠራ ውጤቶች ናቸው። ግጥሞቹ ደራሲያቸው ስለማይታወቅ ህዝባዊ ሀብት ናቸው። የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ብዙ ናቸው። የዐውዳመት፣ የፉከራ፣ የልመና፣ የሙሾ፣ የሥራ ግጥሞች...ወዘተ. ሁሉ የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ናቸው። ቃላዊ ግጥሞች እንደየሁኔታው ሊዜሙ ወይም በእንጉርጉሮ ሊቀርቡ ይችላሉ። ቃላዊ በመሆናቸው በአብዛኛው አጫጭር ናቸው። እነዚህ ቃላዊ ግጥሞች ምጣኔ፣ ምትና ዜማ አላቸው። ግጥሞቹ በአብዛኛው በእኩል ጊዜ እንዲያልቁ ሆነው የተመጠኑ ሐረጋት ይይዛሉ። የተመጠኑት ሐረጋት በተወሰነ ጊዜ ሲደጋገሙ ደግሞ ምት ይፈጥራሉ። ሲነበቡም ዜማ አላቸው። ግጥሙ እንደሚገልጸው ስሜት ዜማው ይለያያል።

ቃላዊ ግጥሞች በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው። የአንድ ማህበረሰብ ባህል በቃላዊ ግጥሞች አማካይነት ጎልቶ ይወጣል። የማህበረሰቡ የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ ወዘተ. ልማድ በግጥሞቹ ይተላለፋል። ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸው አመለካከት፣ እምነትና ፍልስፍና ሁሉ በቃላዊ ግጥሞች ይንፀባረቃል። በጥቅሉ የሰው ልጆች ማንነት በራሳቸው ቃላዊ ግጥሞች ይገለጻል።

(አንተነህ። 2001። የአማርኛ ሥነቃል አጭር ቅኝት እና ዘሪሁን። 1992። የሥነጽሑፍ መሠረታውያን። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

## ክፍለጊዜ ሁለት

# የአጨዳ ጊዜ



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።**

1. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁት ለቡድን አባሎቻችሁ ንገሩ።
2. ሰዎች ሥራ በሚሠሩበት ጊዜ የሚገጥሟቸው ቃላዊ ግጥሞች በምን በምን ላይ ያተኩራሉ?
3. የምታውቁትን የሥራ ቃላዊ ግጥም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፤ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍም ተናገሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አዳዲስ ቃላትና ሐረጋትን በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና ጥንድ ጥንድ በመሆን በፍቺያቸው ላይ ተወያዩ።
2. “ሻሽ የጠመጠመች” ማጭድ ሲል ምን ለመግለጽ ይመስላችኋል?

ክፍለጊዜ ሦስት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ግጥም መሠረት በጽሑፍ መልሱ።**

1. የጎበዝ ማጭድ በምን በምን ይታወቃል?
2. ገጣሚው "እንዳዘንተኛ ፊቷን ፊጅታለች" ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
3. በግጥሙ መሠረት አርሶ አደሩ ማጭዱን የሚያሞግሰው ለምን ይመስላችኋል?
4. የግጥሙ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ንግግር ለማድረግ የሚያስችላችሁ ተግባር ቀርቧል። ስለዚህ የቀረበውን ተግባር መሠረት በማድረግ ንግግር ታደርጋላችሁ።

### ተግባር አንድ

በአካባቢያችሁ በእርሻ፣ በአጨዳ፣ እና በውቂያ ጊዜ የሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ በቃል ዘገባ አቅርቡ።

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ክፍለጊዜ አምስት**

ቀጥሎ "የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥም" በሚል ርዕስ ቃላዊ ግጥም ቀርቦላችኋል። ግጥሙን ካነበባችሁ በኋላ የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች ሥሩ።

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ስዕሉን በመመልከት ከስዕሉ የተረዳችሁት ለቡድን አባሎቻችሁ ተናገሩ።
2. ሰዎች በእርሻ ጊዜ የሚገጥሟቸው ቃላዊ ግጥሞች በምን በምን ላይ ያተኩራሉ?
3. የምታውቋቸውን ቃላዊ ግጥሞች በማዜም ወይም በማንበብ አቅርቡ፤ ጭብጡንም ተናገሩ።

**የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥም**

እኔስ ደስ ይለኛል የግብርና ኑሮ፣
ወተቱ ከማጀት እሸቱ ከጓሮ።
እስኪ ቅመሱልኝ የማረሻን ለዛ፣
እህል ካልቀመሱ ከንፈርም አይወዛ፣
እርጎ ተደፍቶ ኮከብ ቢመስል፣
እኔስ አልሰርቅም ውሻ ይመስል።
ሞቼ እገኛለሁ ከእርሻው ስር፣
ሞቼ እገኛለሁ ከድንበሩ ስር።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ግጥሙን ስታነቡ ያጋጠሟችሁን አዳዲስ ቃላት በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡
2. እስካሁን ካነበባችኋቸው ስንኞች የተረዳችሁትን ፍሬ ነገር ተናገሩ፡፡

እኔስ አርሳለሁ አላማርርም፣
ችግር በወንጭፍ አይባረርም።
ካልረባ ሹመት ይሻላል እርሻ፣
ሰርዶ ዘርጋፊ በሹል ማረሻ።
ማረስ ነው እንጂ እጅ እስኪተላ፣
አሻግረው ቢያዩት የሰው ጎተራ፣
ጥም አይከለክል ረሀብ አይከላ።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. "እኔስ ደስ ይለኛል የግብርና ኑሮ" የተባለው ለምን ይመስላችኋል?
2. ገጣሚው "እኔስ አርሳለሁ አላማርርም፣ ችግር በወንጭፍ አይባረርም።" ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

3. በግጥሙ መሠረት አርሶ አደሩ ማረሻውን የሚያሞግሰው ለምን ይመስላችኋል?
4. የሰውን እጅ ማየት አስፈላጊ አለመሆኑን የሚያሳየው ስንኝ የትኛው ነው?
5. የግጥሙ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ለ. በቃላዊ ግጥሙ መሠረት ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ አቅርቡ።**

1. ወንጭፍ
2. ሹመት
3. ለዛ
4. ማረሻ
5. አይከላ
6. ጎተራ
7. ሰርዶ ዘር ጋፊ
8. እጅ እስኪተላ

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## አቀላጥፎ ማንበብ

**ማስታወሻ**

ግጥም የሚዋቀረው ሐረግ በሐረግ ነው። ሐረጎች ደግሞ ስንኝን ይመሠርታሉ። ሐረግ በግጥም ውስጥ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ ሲሆን ስንኝ ደግሞ አንድ የግጥም መስመር ነው። አንድን ግጥም አቀላጥፎ ለማንበብ የሚረዱ መመሪያዎች:-

- በሐረጎችና በስንኞች መጨረሻ የተወሰነ የጊዜ ቆይታ ማድረግ፣

- ግጥሙን በተገቢ ዜማዊ ቃና ማንበብ፣
- የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶችን ከመምህራን፣ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን፣ ከሥነጽሁፋዊ መድረኮች ወዘተ. ማዳመጥ

ግጥሙ የቅስቀሳ፣ የሐዘን፣ የግርምት፣ የትዝብት፣ የውደሳ፣… መሆኑን በማጤን የአነባበብ ለዛውን እንደየግጥሙ ዓይነት እየቀያየሩ ለማንበብ መሞከር ያስፈልጋል።

**ተግባር ሁለት**

1. መምህራችሁ ባሳዩአችሁ የግጥም አነባበብ ስልት መሠረት “የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥሞች” በሚል ርዕስ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም ዜማዊ ቃናቸውን በመጠበቅ በየተራ አንብቡ።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

2. የግጥም አነባበብ ስልቶችን በመጠቀም “የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች” በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም በግላችሁ ድምጽ እያሰማችሁ አንብቡ።

**የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች**

እያት ያችን ወጣት ያንገቷን ንቅሳት፣
አሁን ቁንጅናዋን ማነው የሚደርሳት።
ያንገቷ ንቅሳት አለው እርከን እርከን፣
የአንቺ እናት ይውለዱ ህዝባዳሙ ይምከን።

እዩት ተመልከቱት ያንገቷን ሥራሥር፣
የተወለወለ በልጅግ የሚመስል።
ዝንጀሮ በገደል ይላል ድኩም ባሌ፣
ያንገቷ ንቅሳት ያስለውጣል በሬ።
አንገትሽ ዝንጉርጉር ቁመናሽ ዘንግ ነው፣
ባክሽ ሰላም በይኝ ሽግዬ ምንድን ነው።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**ክፍለጊዜ አስር**

በዚህ ትምህርት ግጥም ለመጻፍ የሚረዳችሁ መልመጃና ተግባር ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሠረት ሥሯቸው።

### መልመጃ ሦስት

**የሚከተሉትን የግጥም ሐረጋት በትክክለኛ አሰዳደር በማደራጀት ግጥሙን አስተካክላችሁ ጻፉ።**

ምሳሌ፡

| የተፋለሰ | የተደራጀ |
|---|---|
| በየገደሉ ሥር/ ዝሩ ምስር፣ በአንድ ቁና ምስር/በቅሎ ተገዛ አሉ። | ዝሩ ምስር በየገደሉ ሥር፣ በቅሎ ተገዛ አሉ በአንድ ቁና ምስር። |

1. ይውላል ከጥላ/ተላላው ገበሬ፣
   ብር ከመሬት ሲፈላ/ውርጭ የመሰለ።
2. የምስሩን ተራ/አላየኸውም ወይ፣
   ሺልንጉ ሲፈላ/እንደክረምት አግቢ።

3. ግፍ አትናገሪ/ኧረ ተይ ዝንጀሮ
   አውድማ ስትጭሪ/አሁን ትገኛለሽ።
4. ልቤን ቆረጥሽው/ኧረ ተይ ዝንጀሮ
   ሰብሌን ጨረስሺው/ለፍቼ ለፍቼ።
5. ምላ ተማምላ/ዝንጀሮ ታረቀች
   ገብሱን ልትበላ/ማሽላውን ትታ

## ክፍለጊዜ አስራአንድ

**ተግባር ሦስት**

1. በተራ ቁጥር 1 እና 2 አስተካክላችሁ የጻፋችኋቸውን ግጥሞች ጭብጣቸውን በሦስት ዓረፍተነገር ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍለጊዜ አስራሁለት

2. ከተራ ቁጥር 3 እስከ 5 የቀረቡትን ግጥሞች ጭብጣቸውን በሦስት ዓረፍተነገር ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍለጊዜ አስራሦስት

3. በትምህርት፣ በእርሻ፣ በሠርግ፣ በአጨዳ፣ ወይም በውቂያ ላይ ከሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች አንድ መርጣችሁ የራሳችሁን ባለአራት ስንኝ ቃላዊ ግጥም ጽፋችሁ በክፍል ውስጥለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**ክፍለጊዜ አስራአራት**

ቀጥሎ የቃላትን ተቃራኒ ፍቺ እንድትለዩ የሚያስችላችሁ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ በትዕዛዞቻቸው መሠረት በትኩረት ሥሯቸው።

### መልመጃ አራት

**ሀ. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ተቃራኒ የሆኑትን ለይታችሁ አውጡ።**

ለምሳሌ፡ መሃል-ዳር

| | | | |
|---|---|---|---|
| መሃል | ጥላቻ | ተቃውሞ | ዳር |
| ድጋፍ | በኋላ | ዋዜማ | በቃል |
| በፊት | ማግስት | በጽሑፍ | አልፎ አልፎ |
| ፍቅር | ዘወትር | የማይታወቅ | ዝርው |
| ጠቀሜታ | ግጥም | ጉዳት | |

**ክፍለጊዜ አስራአምስት**

**ለ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ትክክለኛ ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ______1. የተለመደ | ሀ. ዝርዝር |
| ______2. ማስማማት | ለ. ማቀናጀት |
| ______3. እምቅ | ሐ. አዲስ |

———4. ጠቃሚ መ. ጎጂ

———5. ግጥም ሠ. ማፋለስ

ረ. ዝርው

**ክፍለጊዜ አስራስድስት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስዉ

በዚህ ትምህርት የጊዜ ተውሳከግሶችን የምትለዩበት ማስታወሻና መልመጃ እንዲሁም በዓረፍተነገር ውስጥ ህዝባርንና ቅንፍን ለመጠቀም የሚስችላችሁ መልመጃ ቀርበዋል። በመሆኑም በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሠረት ሥሯቸው።

### ማስታወሻ

ተውሳከግሶች ግስን ቀድመው በመግባት ስለግሱ የሚገልጹ (የሚያጎላምሱ) ናቸው። በሌላ አገላለጽ ተውሳከግሶች በዓረፍተነገር የሚገለጸውን ድርጊት (ግሱን) ይበልጥ የሚልገጹ ቃላት ናቸው። በዚህም የግሶች ጭማሪ ተብለው ይታወቃሉ። ግሱን ከሚገልጹባቸው ሁኔታዎች አንዱ ከጊዜ አንጻር ነው። እንደዚህ ዓይነት ተውሳከግሶችም የጊዜ ተውሳከግሶች ተብለው ይጠራሉ።

ለምሳሌ፡ ፍራያል በጠዋት ሄደ።

የተሠመረበት ቃል "ሄደ"ን (ግሱን) ከጊዜ አንጻር የሚገልጽ ነው። ስለዚህ የጊዜ አመልካች ተውሳከግሶች ከጊዜ አንጻር ግሶችን የሚገልጹ ቃላት ናቸው።

## መልመጃ አምስት

**ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የጊዜ አመልካች ተውሳከግስ የሆኑትን ቃላትና ሐረጋት ለይታችሁ ጻፉ።**

ምሳሌ: ልጁ <u>ትናንት</u> ወደ ቤቱ ሄደ።

በዚህ ዓረፍተነገር “ትናንት” የሚለው ቃል የጊዜ ተውሳከግስ ነው።

1. ጫላ አሁን ይመጣል።
2. ለሊሴ ቶሎ መጣች።
3. አህመድ የተሰጠውን ዕቃ ዛሬ አስረከበ።
3. አስቴር ፈተና ቦታ ገና አልደረሰችም።
4. ዘሀራ ወደ ትምህርት ቤት ዛሬ ማታ ሄደች።
5. ዝናቡ ሳይመጣ በጧት ወደ ቤታችን መሄድ አለብን።

**ክፍለጊዜ አስራሰባት**

**ለ. የሚከተሉትን የግዜ አመልካች ተውሳከግሶች በመጠቀም ዓረፍተነገር መሥርቱ።**

| | | |
|---|---|---|
| ትናንት | ዘውትር | ቅድም |
| በማለዳ | ነገ | ማታ |

**ክፍለጊዜ አስራስምንት**

**ሐ. የሚከተሉትን ሥርዓተነጥቦች በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።**

**ለምሳሌ፡ ልጁ ወደት/ቤት ሄደ።**

ወደ ሀዋሳ ለመሄድ መኪና (አውሮፕላን) መጠቀም ይቻላል።

ሀ. ህዝባር (/)

ለ. ቅንፍ ( )

# ምዕራፍ አራት

# ዘመናዊ ግብርና

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ጽሑፍን አዳምጣችሁ ቃላዊ ምላሽ ትሰጣላችሁ፤
- አመዛዛኝ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- ጊዜ አመልካች ተውሳከ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር ትመሠርታላችሁ፤
- የቃላት ፍቺ ለመስጠት አብሮ ሂያጅ ቃላትን ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት "ግብርና በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረትም የቀረቡትን ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# ግብርና በኢትዮጵያ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. በሀገራችን የሚካሄደው ግብርና ምን ዓይነት ነው?
2. በግብርና ሥራዎቻችን መሻሻል የሚገባቸውነገሮች አሉ? ካሉ የትኞቹ መሻሻል እንዳለባቸው ተወያዩ።
3. የዘመናዊ ግብርና መገለጫዎች ምንምን ይመስሏችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ያጋጠሟችሁን አዳዲስ ቃላትና ሐረጋት በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና በፍቺያው ላይ ተወያዩ።
2. ባዳመጣችሁት መሠረት ደካማ የሥራ ባህል እንዳለን የሚያመለክቱ ጉዳዮችን ምንምን እንደሆኑ ተናገሩ።

ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. “ደካማ የሥራ ባህል” ሲል ምን ለማለት ነው?
2. ኢትዮጵያ ያላት ተስማሚ የአየር ንብረት የሚያበቅላቸው ምንምን እንደሆኑ ጥቀሱ።
3. ጠባቂና ኋላቀር ያደረገን ምንድነው?
4. በምዕራባዊያን የምንረዳው ለምን ይመስላችኋል?
5. የጽሑፉን ዋና መልዕክት በአጭሩ አስረዱ።

ክፍለጊዜ ሦስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ባዳመጣችሁት መሠረት የጽሑፉ ዋና መልዕክት ላይ ውይይት የምታደርጉበት ተግባር ቀርቦላችኋል። ስለዚህ ተግባሩን በትዕዛዙ መሠረት ሥሩ።

**ተግባር አንድ**

“ግብርና በኢትዮጵያ” በሚል ርዕስ የተነበበላችሁ ጽሑፍ ዋና መልዕክቱ ምን እንደሆነ በቡድን ተወያዩ፡፡ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ዘገባ አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ቀጥሎ "ውጤታማ የስንዴ አመራረት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ፣ ሀሳቡን መረዳታችሁን ለማረጋገጥ ራሳችሁን ጥያቄ በመጠየቅ ድምፅ ሳታሰሙ ታነባላችሁ። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቻቸው መሠረት ሥሯቸው።

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላትና ሀረጋት በቃል ፍቺስጡ።**

1. ማነቆ
2. ንጥረነገር
3. ዝርያ
4. አረም
5. በብተና መዝራት

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ውጤታማ የስንዴ አመራረት



ስንዴ በኢትዮጵያ ደጋ እና ወይናደጋ አካባቢዎች በብዛት ይመረታል። በኢትዮጵያ በዋናነት የሚመረቱ የስንዴ አይነቶች ሁለት ናቸው። እነሱም የዳቦ ስንዴ እና የመኮረኒ ስንዴ በመባል ይታወቃሉ። ምንም እንኳን የስንዴ ጠቀሜታ ከፍተኛ ቢሆንም ምርታማነቱ በሀገራችን በጣም ዝቅተኛ ነው። ለዚህም አስተዋፅኦ የሚያደርጉ በርካታ ማነቆዎች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ አርሶ አደሩ የሚጠቀምባቸው ያልተሻሻሉ ዝርያዎች እንደዋነኛ ምክንያት ይጠቀሳሉ። ዝርያዎቹ ምርታማነታቸው ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ በሽታን መቋቋም የማይችሉ ናቸው።

ሌላው ደግሞ በአብዛኛው አርሶአደሮቻችን ዘንድ ያልተሻሻለ የአመራረት ዘዴ መጠቀም ነው። ያልተሻሻለ አመራረት ስንል ዘር በብተና መዝራትና ትክክለኛውን የዘር መጠን አለመጠበቅ ይገኙባቸዋል። የአፈር ለምነት **መሟጠጥ**፣ አረም፣ የበሽታዎችና **ተባዮች** መከሰት እና ተገቢ የአረም መድኃኒት አለመኖር ለምርታማነታችን መቀነስ የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው። አረሞች የሰብሉን ቦታ፣ የፀሓይ ብርሃን፣ ውኃና አየር እንዲሁም የምግብ ንጥረ ነገሮችን ይሻማሉ። እንዲሁም በሰብል ላይ አላስፈላጊ የሆነ ጎጂ ንጥረነገሮችን በሥሮቻቸው አማካኝነት በመልቀቅ ዕድገታቸውን ይገታሉ። በተጨማሪም አረሞች ከምርት ቅነሳ አልፈው የሰብል ምርት ጥራትን በመቀነስ በገበያ ተፈላጊነትን ይቀንሳሉ።

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች የተረዳችሁትን ፍሬ ነገር ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. ካነበባችኋቸው አንቀጾች በመነሳት ቀጥሎ የሚመጣውን ሐሳብ ገምቱ።

ስለዚህ ከፍተኛ ምርትና ጥራት ያለው ስንዴ ለማምረት ተስማሚና ትክክለኛ ዝርያ መምረጥ ያስፈልጋል። ነገር ግን ዝርያውን መምረጥ ብቻውን የሁሉም ውጤት ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። ውጤታማና ትርፋማ የሆነ የስንዴ ምርት ለማግኘት ተስማሚ የአየር ንብረት፣ የማሳ ዝግጅት፣ እንክብካቤዎችን እና መሰል ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ከማሳ መረጣ አንጻር በጣም ተዳፋታማ ያልሆነ መሬት መምረጥ አስፈላጊ ነው። መሬቱም ለምነቱን ያላጣና አቀማመጡ ወጥነት ያለው መሆን አለበት። ማሳውም የለሰለሰና በወቅቱ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል። የለሰለሰ ማሳ በአፈር ውስጥ የአየርና የውሃ እንቅስቃሴን ያሻሽላል። የተለያዩ የአረም ዘሮችን ለመቆጣጠርም ያስችላል። በአጠቃላይ የሀገራችንን የስንዴ ምርታማነት የሚቀንሱ ብዙ ምክንያቶች አሉ። እነዚህን ችግሮች ቀርፈን የስንዴ ምርቶቻችንን ማሻሻል ይኖርብናል። ምርታማነታችን ሲጨምር የሀገር ውስጥ ፍላጎታችንን ከማርካት አልፎ ለውጭ ምንዛሪ ማግኛ ልንጠቀምበት እንችላለን።

(አስረሴ ሀሰን እና ሌሎች (2008) የዳቦ ስንዴ አመራረት መመሪያ BDU-CASCAPE working paper 15)

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት ምክንያት እየሰጣችሁ በቃል መልሱ።**

1. ለስንዴ ምርታችን መቀነስ አንዱ ምርጥ ዘር መጠቀማችን ነው።
2. ስንዴ በአብዛኛው በቆላማ አካባቢዎች ይመረታል።
3. የለሰለሰ ማሳ አረም ለመከላከል ይረዳል።
4. የአረም መድኃኒት አለመኖር ምርታመነትን ይቀንሳል።
5. ተስማሚና ትክክለኛ ዝርያ መምረጥ ብቻውን ጥራት ያለው ምርት ለማምረት ያስችላል።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።**

1. ስንዴ በኢትዮጵያ በብዛት የሚመረተው በየትኛው የአየር ንብረት ዓይነት ነው?
2. አረም የስንዴ ምርታማነትን የሚቀንሰው እንዴት ነው?
3. የስንዴ ምርታማነትን ለመጨመር ምንምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. የስንዴ ምርታማነትን የሚቀንሱ ነገሮች ምንምን ናቸው?
5. "ለውጭ ምንዛሪ ማግኛ ልንጠቀምበት እንችላለን።" የሚለው ሀሳብ ምንን ያመለክታል?

6. በአንደኛው አንቀጽ “ለዚህም አስተዋፅኦ የሚያደርጉ በርካታ ማነቆዎች አሉ።” ሲል ምን ለማለት ነው?

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ሐ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

ለምሳሌ፡ መቋቋም - በበሽታ በቀላሉ የማይጠቃ

1. መሚጠጥ
2. መልቀቅ
3. ተባይ
4. ለም
5. የለሰለሰ ማሳ

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሠረት ሥሩ።**

ምሳሌ፡ ተሰበረ ብለን ተሰባበረ፣ ስብርባሪ፣ መሰባበር ካልን

1. ፈረሰ
2. ተናገረ
3. ታነቀ
4. ታሰረ
5. ተቀናበረ
6. ተመረጠ

**ክፍለጊዜ አስር**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት አመዛዛኝ አንቀጽለመጻፍ የሚያስችላችሁ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። በመሆኑም ቀጥሎ የቀረቡላችሁን ተግባራት በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሠረት ሥሯቸው።

**ማስታወሻ**

አመዛዛኝ ድርሰት (አከራካሪ ድርሰት) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሐሳቦችን የትኛው እንደሚሻል በማመዛዘን አሳማኝ ነጥቦችን እያቀረበ የሚያስረዳ ነው። ለምሳሌ ከገጠር እና ከከተማ ኑሮ የትኛው እንደሚሻል በማመዛዘን ማስረዳት ይቻላል።

**ክፍለጊዜ አስራአንድ**

**ተግባር ሁለት**

1. ከባህላዊና ከዘመናዊ ግብርና የትኛው የተሻለ እንደሆነ አመዛዛኝ ድርሰት ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

**ክፍለጊዜ አስራሁለት**

2. ከአባት እና ከእናት ማን የበለጠ ኃላፊነት እንደሚሸከም አመዛዛኝ ድርሰት ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

**ክፍለጊዜ አስራሦስት**

3. ከመኪና እና ከብስክሌት የትኛው የተሻለ እንደሆነ አመዛዛኝ ድርሰት ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

**ክፍለጊዜ አስራአራት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት አብሮ ሂያጅ ቃላትን መጠቀም የምትችሉበት መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት በትኩረት ሥሯቸው።

**መልመጃ ሦስት**

**ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት በባዶ ቦታዎች ላይ አብሮ ሂያጅ ቃላትን መርጣችሁ ፍቺ እንዲሰጥ አድርጋችሁ አሟሉ።**

ለምሳሌ፡ ልጁ ወደትምህርት ቤት ሄደ።

ሀ. ስለ ለ. ወደ

ሐ. ከ መ. እንደ

1. ለሊሴ ወደገበያ ——— ትፈልጋለች።

ሀ. መሄድ ለ. መውጣት

ሐ. መሥራት መ. ሀ እና ለ

2. ዳኞቹ ለችሎት ——— ።

ሀ. ተሰይመዋል ለ. ተለቀዋል

ሐ. ተከፍተዋል መ. ተቀምጠዋል

3. የዛሬው መርሃግብር በስኬት ——— ።

ሀ. ሄዷል ለ. ተዘግቷል

ሐ. ተጠናቋል መ. ለእና ሐ

4. ሰውዬው በጣም ——— ቤት ገዛ።

ሀ. ጥቁር ለ. ትልቅ

ሐ. ወፍራም መ. አጭር

## ክፍለጊዜ አስራአምስት

**ለ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሠረት አብሮ ሂያጅ ቃላትን በመጠቀም በጽሑፍ መልሱ።**

**ለምሳሌ፡**

"ዳቦ ይደፋል፤ ካልን እንጀራ ይጋገራል" እንላለን።

1. ለወተት ስልባቦት ካልን ለጠላ ________።
2. ጠላ ይጠመቃል ካልን ጠጅ ________።
3. ለጠጅ አምቡላ ካልን ለጠላ ________።
4. ንፍሮ ይቀቀላል ካልን ቆሎ ________።
5. ቆሎ ይቆረጠማል ካልን ጫት ________።
6. የአንበሳ ልጅ ደቦል ከተባለ የድመት ልጅ ________ ይባላል።
7. የአህያ ልጅ ውርንጭላ ከተባለ የፈረስ ልጅ ________ ይባላል።
8. ለዶሮ ይጮኻል ካልን ለአህያ ________ እንላለን።
9. ለጅብ ይጮኻል ካልን ለአንበሳ ________ እንላለን።
10. ላም ጥጃ ወለደች ካልን ዶሮ ________ እንላለን።

**ክፍለጊዜ አስራስድስት**

**ሐ. ከላይ በ"ለ" ላይ በሠራችሁት መሠረት ሌሎች አብሮ ሂያጅ ቃላትን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**ክፍለጊዜ አስራሰባት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት የጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን እንድትለዩ የሚረዳችሁ መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በምዕራፍ ሦስት የተሰጣችሁን ማስታወሻ ደግማችሁ በማንበብ መልመጃውን በትዕዛዙ መሠረት ሥሩ።

**መልመጃ አራት**

**ሀ. የሚከተሉትን የጊዜ አመልካች ተውላጠ ስሞች በመጠቀም ዓረፍተነገር መሥርቱ።**

1. ዛሬ
2. ቶሎ
3. አሁን
4. በሌሊት
5. ጧት

**ክፍለጊዜ አስራስምንት**

**ለ. የተለያዩ ጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን በመጠቀም አስር ዓረፍተነገር ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

# ምዕራፍ አምስት

## ቱሪዝም

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ቃላትን ወደ ምዕላዶች መነጣጠልን ትተገብራላችሁ፤
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- ሀላፊ ጊዜን በመጠቀም አንቀፅ ትጽፋላችሁ፤
- ድኅረ ቅጥያዎችን ትጠቀማላችሁ፤
- የተዘጋጀን ፅሑፍ ለመረዳት ራስመር ብልሃቶችን ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት "ወንጪ ሐይቅ" በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረትም የቀረቡትን ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# ወንጪ ሐይቅ



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ስጡ።

   ሀ. መስህብ          ሐ. አምባ

   ለ. ደሴት

2. የምታውቋቸውን የቱሪስት መስህቦች ተናገሩ።
3. ከዚህ በፊት ስለወንጪ ሐይቅ የምታውቁትን ተናገሩ።
4. የቱሪስት መስህብ ጥቅሞችን ግለጹ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አዳዲስ ቃላትና ሐረጋትን በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና በፍቺያቸውን ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።
2. የወንጪ ሐይቅ ከአምቦ ከተማ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

## ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. የሚከተሉትንጥያቄዎችበቃልመልሱ።**

1. የወንጪ ሐይቅ ምን ያህል ሰፋትአለው?
2. የወንጪ ሐይቅ የቱሪስት መዳረሻ እንዲሆኑ ምንምን ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል?
3. የወንጪ ሐይቅ ጥልቀት ምን ያህል ነው?
4. በሐይቁ መካከል ስንት ደሴቶች አሉ?
5. ያዳመጣችሁት ምንባብ መልዕክት ባጭሩ አብራሩ።

## ክፍለጊዜ ሦስት

**ለ.ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በምዕላድ ደረጃ በመነጠል አመልከቱ።**

**ለምሳሌ፡** ነገሮች፡ ነገር-ኦች

1. ፍልውሃዎችም
2. ደሴቶች
3. በተራራዎች
4. ከመድረሳችን
5. ፈዋሾች

## ክፍለጊዜ አራት

**ሐ. በ “ለ” ሥር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች ቃላት በመፈለግ ቃላቱን በምዕላድ ደረጃ በመነጠል አመልከቱ።**

## ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ንግግር ለማድረግ የሚያስችሏችሁ ተግባራት ቀርበላችኋል። ስለሆነም ትዕዛዙን መሠረት በማድረግ ንግግር አድርጉ።

**ተግባር አንድ**

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ሰዎችን በመጠየቅ ወይም በማንበብ ተዘጋጅታችሁ አጭር ንግግር አድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

2. አንድን ሐይቅ የመጎብኘት ዕድል ቢያጋጥማችሁ ምን ዓይነት ቅድመዝግጅት እንደሚያስፈልግ ሰዎችን በመጠየቅ ለጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ?

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ቀጥሎ "የነጭ ሣር ፓርክ" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሯቸው። ስታነቡም በምንባቡ ውስጥ የማታውቋቸውን ቃላትና ሐረጋት እየጻፋችሁና ሀሳቡን እየተረዳችሁ በየግላችሁ አንብቡ።

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና በቃል መልስ ስጡ።**

1. ፓርክ ማለት ምን ማለት ነው? በውስጡስ ምን ምን ነገሮችን ይይዛል?
2. የምታውቁትን ፓርክ በመጥቀስ የት እንደሚገኝ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

# የነጭ ሣር ፓርክ

በኢትዮጵያ ከ15 የማያንሱ ፓርኮች ይገኛሉ። ከእነዚህ ፓርኮች መካከል አንዱ ነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ ይባላል። የነጭ ሳር ብሔራዊ **ፓርክ** በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል በአማሮ ወረዳ ውስጥ ይገኛል። ፓርኩ በ1974 ዓ.ም ተመሠረተ። ስያሜውን ያገኘው በውስጡ ባለው ነጭ የሣር ዓይነት ነው። ፓርኩ ከፊንፊኔ 510 ኪሎሜትር ይርቃል። **ፓርኩን** በምሥራቅ የአማሮ ተራራዎች፣ በሰሜን የአባያ ሐይቅ፣ በደቡብ የጫሞ ሀይቅ **ያዋስኑታል**። በሁለቱ ሀይቆች መካከል ደግሞ "የእግዜር ድልድይ" እየተባለ የሚጠራ ተራራ ይገኛል። ፓርኩ የተመሠረተው በውስጡ ያሉትን የዱር እንስሳትና **ምቹ** የመኖሪያ አካባቢያቸውን ለመጠበቅ ነው። በፓርኩ ውስጥ በርካታ የዱር እንስሳትንና የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ። የተለያዩ የዓሳ ዝርያዎችን በያዙ ወንዞችና ሀይቆችም የተከበበ ነው። በዚህም ምክንያት መስህብነቱ ከፍተኛ ነው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ የት አካባቢ ይገኛል?
2. አንደኛውን አንቀጽ አንብባችሁ ስትጨርሱ በማታውቋቸው ቃላትና ሐረጋት ላይ በጥንድ ተወያይታችሁ ለቃላቱ ፍቺ ስጡ፤ ንባባችሁንም ቀጥሉ።

የፓርኩ ከፍታ 1108-1650 ሜትር ይደርሳል። ሥርማሌና ክንፎ የተሰኙ ሁለት ትላልቅ ወንዞች ፓርኩን አቋርጠውት ያልፋሉ።

በፓርኩ ውስጥ ሰፊ የሣር ሽፋን፣ ቁጥቋጦዎች፣ ደኖች፣ ኮረብታዎችና ተራራዎች ይገኛሉ። ፓርኩ 200 ያህል የአዕዋፍ ዝርያዎችን የያዘ ነው። 37 ያህል **የአጥቢ** እንስሳት ዝርያዎችም ይገኙበታል። ከእነዚህ መካከል የስዋይኔ ቆርኬ፣ የሜዳ አህያ፣ ጉማሬ፣ አዞና የሜዳ ፍየል ዋናዋናዎቹ ናቸው። በሀይቆቹ ውስጥ የተለያዩ የዓሳ **ዝርያዎች** ይገኛሉ። በሀይቁ ምሥራቃዊ ክፍል ደግሞ ፍልውሃ ምንጮች ስለሚገኙ ፓርኩን ተደናቂ ያደርጉታል። እንዲሁም በጫሞ ወንዝ ዳርቻ የሚገኘው የአዞ እርባታ ጣቢያ ለፓርኩ ተጨማሪ መስህብ ሆኖታል። ነጭ ሣር ፓርክ በአንፃራዊነት በከፍተኛ ቦታ ላይ ይገኛል። ከመጓጓዣ፣ ከአስጎብኚ፣ ከቱሪስት መዝናኛና ማረፊያ አንጻርም ነጭ ሣር ፓርክ በተሻለ ተሟልቶለታል ማለት ይቻላል። ስለሆነም ለፓርኩ የመንገድና የቱሪስት ማረፊያሎጂዎችን በመገንባት በቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ ያስፈልጋል።

(የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ድረገፅ፣ 2014)

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ ስያሜውን ያገኘው እንዴት ነው?
2. ነጭ ሣር ፓርክ በአንጻራዊነት መሰረተልማቶች የተሟሉለት የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

3. ፓርኩ መስህብነት እንዲኖረው ያደረጉ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?
4. በጫሞና በአባያ ሀይቆች መካከል ያለው ተራራ ምን በመባል ይጠራል?
5. የጽሑፉ ዋና ሀሳብ ምን እንደሆነ አብራሩ።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

ለምሳሌ፡ ምንጭ - ውሃ የሚገኝበት ጉድጓድ

ሀ. አጥቢ
ለ. ፓርክ
ሐ. ምቹ
መ. ያዋስኑታል
ሠ. ዝርያ

**ክፍለጊዜ አስር**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ሃላፊ ጊዜን ለመለየት የሚያስችላችሁ ተግባራት ቀርቦላችኋል። በመሆኑም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ተግባራቱን በትኩረት ሥሯቸው።

### ተግባር ሁለት

**ሀ. ቀጥሎ ከቀረበው አንቀጽ ውስጥ የሀላፊ ጊዜ አመልካች ግሶችን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

ለምሳሌ፡- ለጥፉለች፣ አቀጣጠለ፣ ....

አንድ እሁድ የተሳፈርኩባት ታክሲ፣ “ሲጋራ ማጨስ አይፈቀድም” የሚል ማሳሰብያ ለጥፋለች፡፡ ታክሲዋን የሚያሽከረክረው ሹፌር ከጥቂት ጉዞ በኋላ ሲጋራ አቀጣጠለ፡፡ ከተሳፋሪው አንዱም ሲጋራ አውጥቶ ነጂውን እንዲለኩስለት ጠየቀው፡፡ ባለታክሲውም ሲጋራውን ሁለት ጊዜ ከሳበ በኋላ “ጽሁፉን ተመልክተሃል?” አለው፡፡ ሁላችንም ርስበርስ ተያየን፡፡ ሲጋራ እንዲለኮስለት የፈለገውም ተሳፋሪ “ታድያ ማሳሰቢያው አንተን አይመለከትም?” ሲለው፣ “ግዴታው የተሰፋሪዎች ብቻ ነው” ብሎ መለሰለት፡፡ የአሽከርካሪው አባባል ለፌዝ የመሰለው ተሳፋሪም “ለፈገግታ የሰነዘርካትን ቀልድ ተውና ሲጋራውን አቀጣጥልልኝ!” አለው፡፡ አንዱ ተሳፋሪ ከጎኑ “ለምን ሰው ግን ቃሉን አይተገብርም” ብሎ በአግራሞት ራሱን ነቀነቀ፡፡

## ክፍለጊዜ አስራአንድ

**ለ. በተግባር “ሀ” በቀረበው ምሳሌ መሠረት አንድ አንቀጽ በሃላፊ ጊዜ አመልካች ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።**

## ክፍለጊዜ አስራሁለት

**ሐ. ከዚህ በፊት አንብባችሁ ከምታውቁት አንድ በሃላፊ ጊዜ ከቀረበ ምንባብ ውስጥ አንድ አንቀጽ ምረጡና በሃላፊ ጊዜ አመልካች የተገለጸበትን አሳዩ።**

ክፍለጊዜ አስራሦስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ለመለየት የሚያስችላችሁ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ስለዚህ በቀረቡላችሁ ትዕዛዛት መሠረት መልመጃውን በትኩረት ሥሩ።

### መልመጃ ሦስት

**ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺያቸውን በጽሑፍ ስጡ።**

1. እባብ
2. ንብ
3. ቤት
4. ተልባ
5. ጉንዳን

ክፍለጊዜ አስራአራት

**ማስታወሻ**

**እማሬያዊ ፍቺ ማለት የቃላት ቀጥተኛ ወይም መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ነው። ፍካሬያዊ ፍቺ ደግሞ ቃሉ ከሚሰጠው ቀጥተኛ ትርጉም በተጓዳኝ ያለ ፍቺ ማለት ነው። ለምሳሌ "ርግብ" ለሚለው ቃል ቀጥተኛ (እማሬያዊ ፍቺው) "የወፍ ዓይነት" ሲሆን ፍካሬያዊ ፍቺው ደግሞ "ሠላም" ወይም "የዋህ" ማለት ሊሆን ይችላል።**

**ክፍለጊዜ አስራአምስት**

**ለ. በ "ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ፈልጉ። ለቃላቱም እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ።**

**ክፍለጊዜ አስራስድስት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ድኅረአምድ ቅጥያዎችን በመለየት መጠቀም የሚያስችላችሁ መልመጃና ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት መልመጃውን በትኩረት ሥሩ።

### መልመጃ አራት

**ሀ. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ድኅረአምድ ቅጥያዎችን ለዩ።**

1. ፈረሶች
2. በሬው
3. መምህራን
4. ቃላት
5. ቤታችን
6. ወንበሩ
7. በጓ
8. ልጅነት
9. ብልጠት
10. ሰውነት

**ክፍለጊዜ አስራሰባት**

**ማስታወሻ**

ቅጥያዎች በቃላት ላይ ካልተቀጠሉ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ (ዓረፍተነገር ውስጥ የማይገቡ) ናቸው። ሲቀጠሉም በቃላት መጀመሪያ ወይም መጨረሻ ላይ ነው። በዚህም

ምክንያት ቅድመአምድ እና ድኅረአምድ ቅጥያዎች ተብለው ይታወቃሉ። ቅድመአምድ ቅጥያዎች ዋናውን ቃል ቀድመው የሚገቡ ሲሆኑ ድህረአምድ ቅጥያዎቹ ደግሞ ከኋላ የሚቀጠሉ ናቸው።

ለምሳሌ፡ ስለሄዱ = ስለ-ሄድ-ኡ

በዚህ ቃል ውስጥ ቅድመአምድ ቅጥያው "ስለ-" ሲሆን ድኅረአምድ ቅጥያው ደግሞ "-ኡ" ነው። ቅጥያዎች ቅድመአምድ ወይም ድኅረአምድ መሆናቸውን የሚያመለክት የሠረዝ ምልክት (-) ከፊት ወይም ከኋላ ይቀመጣል።

## ክፍለጊዜ አስራስምንት

**ለ. የሚከተሉትን ድኅረአምድ ቅጥያዎች በመጠቀም ቃላት መሥርቱ።**

(-ኦች፣ -ኡ፣ -ኧት፣ -ኣችን፣ -ነት፣ -ዋ፣ -ዎች፣ -ን)

# ምዕራፍ ስድስት

# ፀረ አደንዛዥ ንጥረ ነገሮች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ለንባብ ተግባራት ተገቢ የሆኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መርጣችሁ ትተገብራላችሁ፤
- የፅሑፍን መዋቅር ትለያላችሁ፤
- ለእንግዳ ቃላት ከአውዱ በመነሳት ፍቺ ትሰጣላችሁ፤ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- ጅምር አንቀጽ አሟልታችሁ ትጽፋላችሁ፤
- ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ በምትገልፁበት ጊዜ መሸጋገሪያ (አያያዥ) ቃላትን (ሐረጋትን) ትጠቀማላችሁ፤
- ተውላጠስሞችን በዓረፍተነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት “ከሲጋራ የመገለል ጠቀሜታ” በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# ከሲጋራ የመገለል ጠቀሜታ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላት ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ሱስ                                        ሐ. ምጣኔ ሀብት

   ለ. መገለል

2. ከዚህ በፊት ስለሲጋራና አስከፊነቱ የምታውቁትን ተናገሩ።
3. ሲጋራ በሰዎች ሕይወት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምን ይመስላችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አዳዲስ ቃላትን በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና በፍቺያቸው ላይ በጥንድ ተወያይታችሁ ለቃላቱ ፍቺ ስጡ።
2. ሲጋራ ለጤና ጠንቅ የሚሆነው እንዴት ነው?

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. አንድ ሰው ሲጋራን በማጨሱ ለምን ዓይነት በሽታ ሊጋለጥ ይችላል?
2. ሲጋራ ማጨስ ከጤና እክል በተጨማሪ ምን ዓይነት ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ዘርዝሩ?

3. ራሳቸውን ከሲጋራ ሱስ ነጻ ያደረጉ ሰዎች የሚያገኟቸውን ጠቀሜታዎች ዘርዝሩ።
4. ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሀሳብ በአጭሩ ግለጹ።

**ክፍለጊዜ ሦስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት የሚሰጣችሁን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ንግግር ታደርጋላችሁ።

**ተግባር አንድ**

1. በአካባቢያችሁ በሲጋራ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ስለሚያጋጥማቸው ችግሮች በቡድን ተወያዩ፡፡ የደረሳችሁበትንም ሀሳብ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

2. ከሲጋራ ሱስ መገለል ያለውን ጠቀሜታ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም በማንበብ ባገኛችሁት መረጃ ላይ ተወያዩ፡፡ ያገኛችሁትንም መረጃ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ክፍለጊዜ አምስት**

ቀጥሎ "ከጫት መገለል" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ሀሳቡን መረዳታችሁን ለማረጋገጥ ራሳችሁን ጥያቄ በመጠየቅና

ሀሳቦችን ከምታውቁት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ርስበርስ በማዛመድ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ። በቅድመንባብ፣ በንባብና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎችም በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሯቸው።

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. "ከጫት መገለል" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ምን መልዕክት የሚያስተላልፍ ይመስላችኋል?
2. ጫት በሰዎች ላይ ስለሚያስከትለው ጉዳት የምታውቁትን ተናገሩ።

## ከጫት መገለል

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በሱስ ተጠቂ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። ሱሰኝነት ሲጋራ በማጨስ፣ ጫት በመቃም፣ እና የተለያዩ አደንዛዥ ዕፆችን በመጠቀም ይመጣል። ብዙ ሰዎች አንዱ ያደረገውን ለማድረግ ሲሉ ለሱስይጋለጣሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በሱስ ውስጥ ያሉ ጓደኞቻቸውን ፍቅር ላለማጣት ሲሉ በሱስ ይጠመዳሉ። ራስን ባለማወቅና የሱሰኝነትን ጉዳት ባለመገንዘብ በችግሩ ውስጥ የሚገቡም በርካቶች ናቸው። በተለይም ታዳጊ ወጣቶች ሲጋራ ማጨስንና ጫት መቃምን የሥልጣኔና የአዋቂነት ምልክት በማድረግ ይጀምራሉ። ቀስበቀስም ወደሱሰኝነት ይሸጋገራሉ።

ይሁን እንጂ ጫት መቃም በጤና፣ በምጣኔ ሀብትና በማህበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። ጫት የሚቅሙ ሰዎች ጤንነታቸው ይታወካል። ጫት መቃም ለአጭር ጊዜ የመነቃቃትና የደስታ ስሜቶችን ቢፈጥርም እንደገና ወደድብርት፣ መረበሽና ዕብደት ሊያስገባ ይችላል። በሂደትም የሆድና የአንጀት ድርቀት ያስከትላል። የምግብ ፍላጎት እንዲቀንስ ያደርጋል። በተሕዋስያን ምክንያት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከል አቅምን ያሳጣል። ለቲቢና ሄፒታይትስ ለመሳሰሉት በሽታዎች ያጋልጣል። የአፍ ጠረንን ይቀይራል። ጥርስን ያበልዛል። በተጨማሪም የልብ ምትንና የደም ግፊትን ይጨምራል። ጫት ከሚቅሙ እናቶች የሚወለዱ ሕጻናትም በቂ የጡት ወተት አያገኙም። በዚህ ምክንያት ዕድገታቸው ይቀጭጫል። የሥራ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን አላግባብ ያባክናል። ማህበራዊ ግንኙነታቸውም የላላ ይሆናል። ጥሩ ሥነ ምግባር ቢኖራቸውም ማህበራዊ ተቀባይነት አይኖራቸውም። በዚህ የተነሳ ለብቸኝነት ይጋለጣሉ።

በአጠቃላይ ጫት መቃም ጎጂ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በተለይ በጤና፣ በምጣኔ ሀብታዊና በማህበራዊ ሕይወት በርካታ ችግሮችን ይፈጥራል። የሥራ ባህልን ይጎዳል።

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች የተረዳችሁትን በቃል ተናገሩ።
2. እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች እና ቀጥሎ ከምታነቡት አንቀጽ መሠረት ሱሰኝነት ምንምን ነገሮች በመጠቀም እንደሚመጣ ዘርዝሩ።

ስለሆነም በጫት ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ራሳቸውን ነጻ ማውጣት ይኖርባቸዋል። ለዚህም አንዱ መንገድ ራስን ማወቅና ጥሩ ጓደኛ መምረጥ ነው። በተለይም በጫት ሱስ የተጠመዱ ሰዎችን ጓደኛ ማድረግ በማይቅሙ ሰዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ምክንያቱም የጓደኞቻቸውን ፍቅር ላለማጣት ወደማይፈልጉት ድርጊት ሊያስገባቸው ይችላል። ለምሣሌ፣ ጫት ቃሚዎች መቃም ለጓደኞቻቸውም የሚመች መስኳቸው ወደራሳቸው ልምድ እንዲመጡላቸው ይገፋፉቸዋል። ከዚህ ችግር ለመዳን ጓደኛን በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ስለቤተሰብ ማሰብና መወሰንም ራስን ከጫት ሱስ ለማግለል ይረዳል። የጫት ሱስ ቤተሰብንም ሆነ ራስን ለመምራት እንቅፋት ይሆናል። ራስን ለማወቅ ደግሞ ስለራስ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማንነትን መረዳትና ራስን መምራት ያስፈልጋል። ለምሣሌ፣ እኔ ማን ነኝ? ነገ ምን መሆን እፈልጋለሁ? ቤተሰቦቼ ከእኔ ምን ይጠብቃሉ? ዓላማዬን ለማሳካት ምን ማድረግ አለብኝ? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ራስን በመጠየቅ ማንነትን

መረዳት ያስፈልጋል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠትና መተግበር ራስን ከጫት ሱስ የማግለያ መንገድ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ጫት መቃም ያለውን ጉዳት ተገንዝቦ ራሱን ከጫት ሱስ ማግለል ይጠበቅበታል::

**ክፍለጊዜ ስድስት**

**መልመጃ ሁለት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።**

1. የሥልጣኔና የአዋቂነት ምልክት በማድረግ ጫት መቃም የሚጀምሩት ታዳጊ ወጣቶች ናቸው።
2. አንቀጽ አንድ የሚያስተላለፈው መልዕክት ጫት መቃም ስለሚያስከትለው ጉዳቶች ነው።
3. ጫት ከሚቅሙ እናቶች የሚወለዱ ሕጻናት ዕድገታቸው ይቀጭጫል።
4. ከጫት የመገለል አንዱ መፍትሔ ጓደኛን በጥንቃቄ መምረጥ ነው።
5. “መገለል” የሚለው ቃል በገባበት አውድ ሁሉ “መራቅ” የሚለውን ቃል ብንተካ ፍቺውን አያዛባም።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ አውዳዊ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መሥርቱባቸው።**

**ለምሳሌ፡** *መገለል፡ ጫት መቃምን መተው ወይም መራቅ ከሱሰኛ ጓደኛ መገለል ጠቃሚ ነው።*

1. *መጠቀም*
2. *መጠመድ*
3. *መሸጋገር*
4. *መታወክ*
5. *መጋለጥ*
6. እንዲመጡላቸው

## ክፍለጊዜ ስምንት

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።**

1. ጫት መቃም በሰዎች ጤና ላይ እንዴት ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ዘርዝሩ።
2. ጫት ቃሚዎች ማህበራዊ ህይወታቸው የላላ የሚሆነው ለምን ይመስላችኋል?
3. ሰዎች በጫት ሱስ ከመያዝ ራሳቸውን እንዴት ሊጠብቁ ይችላሉ?
4. "<u>በተሕዋስያን</u> ምክንያት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከል አቅምን ያሳጣል።" በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ የተሠመረበት ቃል ምን ማለት ነው?
5. እንዴት ላሉ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ራስን ከጫት ሱስ ማግለል ይቻላል?
6. ከጽሑፉ የተገነዘባችሁት ዋና መልዕክት በአጭሩ አብራሩ።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ጅምር አንቀጽን አሟልታችሁ እንድትጽፉ የሚያስችላችሁ ተግባር ቀርቦላችኋል። በመሆኑም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሥሩ።

**ተግባር ሁለት**

**ቀጥሎ የቀረቡትን አንቀጾች ተገቢውን ሀሳብ በማከል አሟልታችሁ ጻፉ፡፡**

1. ኤድስ ገዳይ በሽታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሽታውን የመከላከያ ዘዴዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ስለታም ነገሮችን በጋራ አለመጠቀም አንዱ ነው፡፡ ስለታም የሚባሉ ነገሮች ደግሞ እንደ መርፌ፣ ምላጭ፣ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህን በጋራ መጠቀም ቫይረሱን ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤናኛው ያስተላልፋሉ፡፡
   ሌላው .......፡፡

ክፍለጊዜ አስር

2. በምህፃረ ቃል “ኮቪድ-19” የሚባለው አዲስ የኮሮና ቫይረስ በመተንፈሻ አካላት ላይ ጉዳት የሚስከትል በሽታ ነው። በመጀመሪያ የተከሰተው ቻይና ውስጥ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሠራጭቷል። ለበሽታው ፈዋሽ መድኃኒት አልተገኘለትም፤ ይሁን እንጂ ለመከላከል የሚያስችሉ በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል አንደኛው ......

ክፍለጊዜ አስራአንድ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ለመስጠት የሚያስችላችሁ መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በምዕራፍ አምስት የተሰጣችሁን ማስታወሻ ደግማችሁ በማንበብ በትዕዛዙ መሠረት ሥሩ።

### መልመጃ ሦስት

**ሀ. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ያላቸውን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በዓረፍተነገር ተጠቅማችሁ አሳዩ።**

**ምሳሌ፡ ጠፋ**

1. እቃው ጠፋ። (እማሬያዊ ፍቺ)
2. ሕጻኑ ያለ ዕድሜው ጠፋ። (ፍካሬያዊ ፍቺ)

“ጠፋ” የሚለው ቃል በ “1” ሥር ያለው እማሬያዊ/ቀጥተኛ ፍቺው የዕቃ አለመገኘትን፣ መሰወርን የሚያሳይ ነው። በ “2” ሥር ያለው ፍካሬያዊ ፍቺ ደግሞ መሞትን ያሳይል።

| | |
|---|---|
| 1. እስስት | 6. እርግብ |
| 2. አውሬ | 7. መርፌ |
| 3. በግ | 8. በረዶ |
| 4. ድንጋይ | 9. ጉቶ |
| 5. አህያ | 10. ምስጥ |

### ክፍለጊዜ አስራሁለት

ለ. በ "ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸውን ቃላት በመፈለግ ፍቺያቸውንም በዓረፍተነገር አሳዩ።

### ክፍለጊዜ አስራሦስት

ሐ. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ያላቸው ፍቺ እማሬያዊ ወይም ፍካሬያዊ ፍቺ መሆኑን ለዩ።

1. ሰውዬው አበባቀጠፈ።
2. ወጣቱ ተቀጠፈ።
3. ልጅቷ ጆሮዋን ተበሳች።
4. ያ ልጅ ጆሮ ነው።
5. ተማሪው እሳት ነው።
6. የጤፍ ዋጋ እሳት ሆኗል።
7. ልጁ እሳት አያያዘ።
8. ሰውዬው አንበሳ ገደለ።
9. አትሌት ሰለሞን ባረጋ አንበሳ ነው።
10. ቋንጣ መብላት እወዳለሁ።

### ክፍለጊዜ አስራአራት

## ምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ስለተውላጠስሞችና አያያዥ ቃላት ምንነት ለመረዳት የሚያስችላችሁ ማስታወሻና መልመጃ ቀርቦላችኋል።

ስለዚህ ማስታወሻውን በትኩረት በማንበብ ጥያቄዎቹን በትዕዛዞቻቸው መሠረት በትኩረት ሥሯቸው።

**ማስታወሻ**

ተውላጠስሞች በስም ምትክ የሚገቡ ናቸው።

ለምሳሌ፡ ናፍያድ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነው።

የሚለውን ዓረፍተነገር "እሱ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነው" ማለት እንችላለን። የተሠመረበት "እሱ" የሚለው ቃል ተውላጠስም ሲሆን ናፍያድ የሚለውን የተጸውዖ ስም ተክቶ የገባ ነው።

**ክፍለጊዜ አስራአምስት**

**መልመጃ አራት**

**ሀ. የሚከተሉትን ተውላጠስሞች በመጠቀም ዓረፍተነገር መሥርቱ።**

ለምሳሌ፡ እኔ - እኔ ዛሬ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ።

| ተ.ቁ | ተውላጠስም | ዓረፍተነገር |
|---|---|---|
| 1 | እኔ | |
| 2 | እኛ | |
| 3 | አንተ | |
| 4 | አንቺ | |
| 5 | እናንተ | |
| 6 | እሷ | |
| 7 | እሱ | |
| 8 | እነሱ | |

## ክፍለጊዜ አስራስድስት

**ለ. በምሳሌው መሠረት በቅንፍ ውስጥ ካሉት ተውላጠስሞች በመምረጥ ዓረፍተነገሩን አሟሉ።**

ምሳሌ፡- ——— ደብተር እንዳስቀምጥለት ጠየቀኝ። (እኔ፣ እሱ)

እሱ ደብተር እንዳስቀምጥለት ጠየቀኝ።

1. ——— ወደገበያ በጧት ሄድን። (እነሱ፣ እኛ)
2. ———ፈጣን ተማሪ ናት። (እሷ፣ አንቺ)
3. ——— ጎበዝ ነጋዴ ናት። (እሷ፣ አንቺ)
4. ———መሬታቸውን ቆፈሩት። (እናንተ፣ እነሱ)
5. ——— በርትተሽ ከሠራሽ ውጤታማ ትሆኛለሽ (አንቺ፣ እሷ)

## ክፍለጊዜ አስራሰባት

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን አሟልታችሁ ጻፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ነገር ግን | ይሁን እንጂ | ስለዚህ |
| ምክንያቱም | ቢሆንም | |
| አለበለዚያ | በተጨማሪም | |

**ማስታወሻ**

አያያዦች በሁለት ነጠላ ዓረፍተነገሮች መካከል እየገቡ የዓረፍተነገሮችን መዋቅር የሚያሳድጉ ቃላት ናቸው። እነዚህም ቃላት፡ ግን፣ እንዲሁም፣ ነገር ግን፣ በተጨማሪም፣ እንጂ፣ እና፣ ስለሆነም፣ ስለዚህም፣ ወዘተ. ያሉ ናቸው።

ምሳሌ፡ የቤት ሥራ ሠርቻለሁ፤ ስለሆነም በክፍል ውስጥ መሳተፍ እችላለሁ።

1. ኳስ መጫወት እወዳለሁ፤——— እንድጫወት አይፈቀድልኝም።
2. የቤት ውስጥ ሥራ በዝቶብኛል፤——— ባለኝ ጊዜ አጠናለሁ።
3. ከትምህርትቤት መቅረት አልወድም፤——— ትምህርት ያመልጠኛል።
4. ገንዘብ ተልኮልኛል፤ ——— ወደባንክ መሄድ አለብኝ።
5. ስለኢትዮጵያ ታሪክ ለማወቅ መጻሕፍትን አንብቡ፤ ——— ትልልቅ ሰዎችን ጠይቁ።
6. ገቢሣ አዲስ ልብስ ተገዝቶለታል፤ ——— ደስተኛ አይደለም።

## ክፍለጊዜ አስራስምንት

ለ. በ “ሀ” ላይ የቀረቡትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም የራሳችሁን ዓረፍተነገር መሥርቱ።

# ምዕራፍ ሰባት

# የጥላቻ ንግግር

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አስተያየቶችን አዳምጣችሁ መስማማትና አለመስማማታችሁን ትገልጻላችሁ፤
- ችግር ለመፍታት የሚያስችላችሁን ሁነት/ጥያቄ ያካተተ የጥላቻ ንግግርን የሚገልፅ ፅሑፍ ታነባላችሁ፤
- ቅፅሎችን ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ፤
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- አንብባችሁ ተመሳሳይ አስረጂ ጽሑፍ ትጽፋላችሁ፤
- "እና" እና "ግን"ን በመጠቀም ድርብ ዓረፍተነገሮችን ትጽፋላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት "የጥላቻ ንግግርና ማህበራዊ መገናኛዎች" በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# የጥላቻ ንግግርና ማህበራዊ መገናኛዎች





## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።**

1. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ፍቺ ስጡ።

   ሀ. የጥላቻ ንግግር　　　　ሐ. በይነመረብ

   ለ ማህበራዊ መገናኛ

2. ከዚህ በፊት ስለማህበራዊ መገናኛ ጠቀሜታና ጉዳት የምታውቁትን ተናገሩ።

3. በአካባቢያችሁ ሰዎች በስፋት የሚጠቀሟቸው የመገናኛ ብዙሃን የትኞቹን ነው? ለምንስ የሚመርጧቸው ይመስላችኋል?

4. እናንተ የምትጠቀሙበት ማህበራዊ መገናኛ አለ? ካለ ምን ጥቅምና ምንስ አስከፊ ነገር እንዳገኛችሁበት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የጥላቻ ንግግር ማለት ምን ማለት ነው?
2. የጥላቻ ንግግር በምን በምን ይገለጻል?

### ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የጥላቻ ንግግር መሠረት የሚያደርገው ምንን ነው?
2. ማህበራዊ መገናኛዎች የጥላቻ ንግግርን በማስፋፋት ረገድ ያላቸው ሚና ምን እንደሆነ ተናገሩ።
3. የጥላቻ ንግግር በሀገር ላይ ምን ዓይነት ጉዳት የሚያስከትል ይመስላችኋል?
4. “አንድነትን መሸርሸር” ሲባል ምን ማለት ነው?
5. ያዳመጣችሁት ምንባብ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

### ክፍለጊዜ ሦስት

**ለ. በሚከተሉት ሀሳቦች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በተወካዮቻችሁ በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

1. “ማህበራዊ መገናኛዎች የጥላቻ ንግግርን ለማስፋፋት አስተዋጽዖ አላቸው” በሚለው ሀሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን ምክንያት እያቀረባችሁ ግለጹ።

### ክፍለጊዜ አራት

2. የቅርብ ጓደኛችሁ በማህበራዊ መገናኛ የሚቀርቡ የጥላቻ ንግግሮችን እየተቀበለ/እየተቀበለች ለሌሎች የሚያስራጭ/የምታሰራጭ ቢሆን/ብትሆን ምን ታደርጋላችሁ?

### ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ንግግር ለማድረግ የሚያስችሏችሁ ተግባራት ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በተሰጣችሁ ተግባራት መነሻነት ንግግር ታደርጋላችሁ።

**ተግባር አንድ**

1. ካዳመጣችሁት ምንባብ የተረዳችሁትን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ።

### ክፍለጊዜ ስድስት

2. የጥላቻ ንግግር በሀገርና በማኅበረሰቡ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በተመለከተ ሰው በመጠየቅ ወይም በማንበብ ያገኛችሁትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ።

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት “የጥላቻ ንግግር መከላከያ መንገዶች” በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሯቸው። ምንባቡንም በለሆሳስ በማንበብ በየአንቀጹ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን በደብተራችሁ ጻፏቸው።

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።**

1. ከዚህ በፊት ስለጥላቻ ንግግር የምታውቁትን ተናገሩ?
2. ሰዎች የጥላቻ ንግግር የሚያንፀባርቁት ለምን ይመስላችኋል?
3. የጥላቻ ንግግርን መከላከል ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

## የጥላቻ ንግግር መከላከያ መንገዶች

የጥላቻ ንግግር ሰዎችን በብሔራቸው፣ በቆዳ ቀለማቸው፣ በሃይማኖታቸው፣ በጾታቸው፣ እና በአካል ጉዳተኝነታቸው በመለየት ከሰዋዊ ክብራቸው ዝቅ ማድረግ ወይም ማዋረድ ነው። ለአብነት ጥቂት የማይባሉ የናዚ አገዛዝ ጀርመናዊያን በወቅቱ ከሌሎች የላቁ እንደሆኑ ራሳቸውን ይቆጥሩ ነበር። በዚህም ምክንያት በርካታ አይሁዶችን እንደተሕዋስያን አድርገው ስለው ነበር። ይህም ውሎ አድሮ ወደ ስድስት ሚሊየን የሚጠጉ

አይሁዶች ላይ ዘግናኝ ግፍ እንዲፈጽሙ አደረጋቸው። በሩዋንዳም ሁቱዎች፣ ለቱትሲዎች ያላቸውን ጥላቻና ንቀት ለመግለጽ "በረሮ" ብለው ይጠሯቸው ነበር። በዚህ አግላይ ፍረጃ ምክንያት በርካቶች ህይወታቸውን አጡ።

እንዲህ ዓይነቱን ማኅበረሰብ የሚያንቋሽሽ የጥላቻ ንግግር አጠራሩንም አንዱ ቡድን በጅምላ ይቀበለዋል። ይህ ዓይነቱ ፍረጃም ሆነ ስያሜ መነሻው እውነት እንዲሆንም አይጠበቅም። ሕዝቡም ሲጋራው በምክንያታዊነት አስቦና አሰላስሎ አይደለም። ስለዚህ እንዲህ ዓይነት በጥላቻ ላይ የተመሠረተ የጅምላ ፍረጃ ማህበረሰቡንም ሆነ ሀገርን ለከፋ ጉዳት ይዳርጋል። ስለሆነም አስተሳሰቡ በ21ኛው ክፍለዘመን ተቀባይነት ስለሌለው የህብረተሰቡን ንቃተህሊና ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ጥቃቶቹን ለመከላከል የሚያስችል የህግ ክልከላ መጣል ተገቢ ነው። ለምሳሌ በበርካታ ሀገሮች የጥላቻ ንግግሮች ሕግ ተደንግጎላቸው ክልከላ ተደርጎባቸዋል። ለምሳሌ በኬንያ ዘርና ጎሳን የሚያጥላላ የጥላቻ ንግግር ማድረግ በሕግ ደረጃ ክልከላ የተጣለበት ወንጀል ነው። እናም በኬንያ የአፍ ወለምታ ለእስር እና ለማህበረሰባዊ ውግዘት ይዳርጋል።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የጥላቻ ንግግር ማለት ምን ማለት ነው?
2. በርካታ አህውዶች በናዚዎች እንደምን ተደርገው ተስለው ነበር?

በሀገራችንም እንዲህ ዓይነት ፍረጃዎችና ስያሜዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተበራከቱ ነው። ይህንንም ለመከላከል በመንግሥት እየተሠሩ ያሉ በርካታ ሥራዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል አዋጅ ቁጥር 1185/2012 አውጥቷል። ለተቋማዊ አፈጻጸሙም ደግሞ ሁለት ተቋማትን ለይቷል። እነዚህም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ናቸው። በሥራ ክትትል ረገድም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የጥላቻ ንግግርን በሚመለከት እንዲሠራ ሲደረግ የብሮድካስት ባለስልጣን ደግሞ የሀሰተኛ ወሬዎችን በሚመለከት እንዲሰሩ በግልጽ ደንግጓል። አዋጁ ላይ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብሮችንም የማዘጋጀት ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በዚህ ሂደት በሀገራችን እየተከሰተ ያለውን የጥላቻ ንግግር ለመከላከል በተለያየ መገናኛ ብዙሃን የሚሠራጩ መረጃዎችን መቆጣጠር ተጀምሯል።

ይሁን እንጂ የጥላቻ ንግግርን መከላከል የመንግሥት ኋላፊነት ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ማኅበረሰቡም በተለይም ወጣቱ

ትውልድ በመገናኛ ብዙሃን የሚሠራጩ መረጃዎችን ትክክለኛነታቸውን አረጋግጦ በመውሰድ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ሀገራዊ ጉዳቶች መቀነስ ይጠበቅበታል።

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐግብሮችን የማዘጋጀት ኋላፊነት የማን ነው?
2. የጥላቻ ንግግር “ሰዋዊ ክብርን ያዋርዳል” ሲባል ምን ለማለት ነው?
3. “የአፍ ወለምታ ለእስር እና ለማህበረሰባዊ ውግዘት ይዳርጋል።” የሚለው ሀሳብ ስለጥላቻ ንግግር ምን የሚያስገነዝብ ይመስላችኋል?
4. የጥላቻ ንግግር በ21ኛ ክፍለዘመን ተቀባይነት የሌለው ለምንድንነው?
5. የጥላቻ ንግግርን መከላከል የማን ድርሻ ነው? ለምን?
6. የምንባቡን ዋና ሀሳብ አጠቃልላችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሠመረባቸው ቃላት በጽሑፍ አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ለምሳሌ፡- አይሁዶች በጀርመንና ሌሎች አገሮች የተሻለ ኑሮ ይመሩ ስለነበር እንደ ጥገኛ ተሕዋስያን ተደርገው ተስለው ነበር።

መልስ፡ ተመስለው ወይም ተመድበው

1. የጥላቻ ንግግር በሕግ ደረጃ ክልከላ የተጣለበት ወንጀል ነው።
2. በጥላቻ ላይ የተመሠረተ የጅምላ ፍረጃ ማህበረሰቡንም ሆነ ሀገርን ለከፋ ጉዳት ይዳርጋል።
3. ሀገራችን የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል አዋጅ አውጥታለች።
4. የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል በመገናኛ ብዙሃን የሚሠራጩ መረጃዎችን መቆጣጠር ተጀምሯል።
5. ወጣቱ ትውልድ በመገናኛ ብዙሃን የሚሠራጩ መረጃዎችን ትክክለኛነት አረጋግጦ መውሰድ ይጠበቅበታል።

**መልመጃ ሦስት**

## ክፍለጊዜ አስር

በ"ሀ" ሥር የተዘረዘሩት ዋና ዋና ሀሳቦች በየትኛው የምንባቡ አንቀጽ እንደተገለጹ ከ"ለ" ሥር በመምረጥ አዛምዱ።

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| ____1 | የጥላቻ ንግግር የሚያስከትለው ጉዳት | ሀ. አንቀጽ ሁለት |
| ____2 | ከወጣቱ የሚጠበቅ ቅድመ ጥንቃቄ | ለ. አንቀጽ አንድ |

——3 ስለጥላቻ ንግግር የተደነገገ አዋጅ　　ሐ. አንቀጽ ሦስት

——4 የጥላቻ ንግግር ምንነት　　መ. አንቀጽ አራት

ሠ.አንቀጽ አምስት

**ክፍለጊዜ አስራአንድ**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት አስረጂ ጽሁፍ ለመጻፍ የሚያስችላችሁ ተግባርና ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። በመሆኑም በማስታወሻው መሠረት በተሰጧችሁ ትዕዛዞች መሠረት ሥሩ።

**ማስታወሻ**

**አስረጂ ጽሑፍ በአንድ ጉዳይ ወይም ነገር ላይ ለአንባቢ ግንዛቤና ዕውቀት ለመስጠት የሚቀርብ ነው። የጸሓፊው ዓላማ ለሌሎች መረጃ ወይም ዕውቀት መስጠት ነው። በመሆኑም ሊጽፍበት የመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ምንነት፣ ፍቺ፣ ወይም ትርጓሜ፣ ጠባያት፣ አገልግሎት፣ ወዘተ. በማስረጃ አስደግፎ የሚያቀርብ ኢ-ልቦለዳዊ የጽሑፍ ዓይነት ነው።**

**ለምሳሌ፡ የኑሮ ውድነት**

**በአሁኑ ወቅት የኑሮ ውድነት እጅግ እየጨመረ በመምጣቱ አብዛኛው የወር ደሞዝተኛ ሊቋቋመው አልቻለም። ለምሳሌ ከሁለት ዓመት በፊት አንድ ሊትር ሠላሳ ብር ይገዛ ነበር። ዛሬ ግን የዘይት ዋጋ በሁለት ዓመት ውስጥ በሦስት እጥፍ አድጓል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የፋብሪካ ወዛደሮች የኑሮ ውድነት መቋቋም እንዳቃታቸው ማሳያዎች አሉ። ለምሳሌ በቅርቡ "ደሞዛችን ይጨመርልን" ሲሉ ያደረጉትን ሠላማዊ ሠልፍ በአስረጂነት መጥቀስ ይቻላል።**

(ደረጄ ገብረ። 1996። ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት። (ገጽ 147-153 ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ))

**ተግባር ሁለት**

1. በትምህርት ሦስት ሥር “የጥላቻ ንግግር መከላከያ መንገዶች” በሚል ርዕስ ከቀረበላችሁ ምንባብ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ያለው የራሳችሁን አንድ አንቀጽ አስረጂ ጽሑፍ ጻፉ።

**ክፍለጊዜ አስራሁለት**

2. ስለማህበራዊ መገናኛና የጥላቻ ንግግር የተጻፈ ጽሑፍ አንብባችሁ ሀሳቡን በማስፋት አንድ አንቀጽ አስረጂ ጽሑፍ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

**ክፍለጊዜ አስራሦስት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት የቃላትን አውዳዊ ፍቺ ለመስጠት የሚያስችላችሁ መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም የቀረበውን መልመጃ በትዕዛዙ መሠረት ሥሯቸው።

**መልመጃ አራት**

**ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር በመሥራት ዐውዳዊ ፍቻቸውን አሳዩ።**

**ለምሳሌ፡**“ልጅቷ እጅግ ውብ ስዕል ሳለች።”በዚህዓረፍተነገርውስጥ “ሳለች” የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺ “ስዕል መሳሏን” የሚያመለክት ሲሆን “ልጅቷ በሞረድ ቢላዋውን ሳለች።” በሚለው ደግሞ “ሳለች”

የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺው "ስለት እንዲኖረው አደረገችው" የሚለውን ያመለክታል።

1. በላኝ
2. ተርታ
3. መስክ
4. ሽምግልና
5. ጠቀመ

## ክፍለጊዜ አስራአራት

**ለ. ቀጥሎ ባሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስጡ።**

**ለምሳሌ፡-**

- በኃይል ስለሮጠች አየር አጠራት። (ትንፋሽ)
- በኦሮሚያ ክልልአየር ማረፊያ ካላቸው ከተሞች አንዱ ጅማ ነው። (አውሮፕላን)

1. ገለባውን ከምርቱ ማጣራት ያስፈልጋል።
2. ስለተፈጸመው ወንጀል ለማጣራት ፖሊስ ወደቦታው አምርቷል።
3. አባይን ለመገደብ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል።
4. የሴት ልጅ ግርዛት እንዳይስፋፋ ጉዳቱን በማስተማር መገደብ ያስፈልጋል።
5. ሰውዬው ገንዘቡን በሥራ ላይ አዋለ።
6. እረኛው ከብቶቹን አንድ ቦታ አዋለ።

**ክፍለጊዜ አስራአምስት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገር ለመመሥረት የሚያስችላችሁ መልመጃ እና ቅጽሎችን ለይታችሁ ለመጠቀም የሚረዳችሁ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በምዕራፍ ስድስት ስለአያያዥ ቃላት የተቀረበላችሁን ማስታወሻ ደግማችሁ በማንበብ መልመጃዎቹን በትዕዛዙ መሠረት ሥሩ።

### መልመጃ አምስት

**ሀ. "እና" እና "ግን"ን በመጠቀም የራሳችሁን አምስት ድርብ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።**

**ለምሳሌ፡** ቀኑ ደመና ነው፤ ግን ዝናብ አልዘነበም።

የሀገራችን የመሬት አቀማመጥ እና የአየር ፀባይ ለኑሮ ተስማሚ ነው።

**ክፍለጊዜ አስራስድስት**

**ለ. ቀጥሎ የቀረቡትን ድርብ ዓረፍተነገሮች በመነጣጠል የተለያዩ ነጠላ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።**

**ለምሳሌ፡** የሳይንስ ትምህርት እወዳለሁ፤ ነገር ግን ጥሩ ውጤት አላስመዘገብኩም። (ይህ ድርብ ዓረፍተነገር ሲሆን ከሚከተሉት ነጠላ ዓረፍተነገሮች የተዋቀረ ነው።)

ሀ. የሳይንስ ትምህርት እወዳለሁ።

ለ. ጥሩ ውጤት አላስመዘገብኩም።

1. አስቴር ትምህርት ቤት ሄዳለች፣ ግን ክፍል ውስጥ

አልነበረችም።

2. ቶሎሳ ተፈጥሮን ማድነቅ ይወዳል፤ግን ልቦለድ ጽሑፎችን አያነብም።
3. መጠለያና ምግብ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ናቸው።
4. እሱ ጠንክሮ አጥንቷል፤ ግን ፈተናውን አላለፈም።
5. የጥላቻ ንግግር በህግ ተከልክሏል፤ ግን አሁንም ሰዎች ከመናገር አልተቆጠቡም።

## ክፍለጊዜ አስራሰባት

### ማስታወሻ

ቅጽሎች ከስም ቀድመው በመግባት ስሙን የሚገልጹ ናቸው። ስሙን የሚገልጹትም በመጠን፣ በመልክ፣ በቁመት፣ በባህርይ፣ ወዘተ. ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ "ጥቁር" የሚለው ቃል ቅጽል ሲሆን ተከትሎት የሚመጣውን ስም መልኩን ወይም ቀለሙን ይገልጻል።

### መልመጃ ስድስት

ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቅጽሎች ለይታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ፡ ረባሽ ተማሪ በክፍላችን አለ። ቅጽሉ "ረባሽ" የሚለው ቃል ነው።

1. ነጭ ሱሪ ለብሶ ነበር።
2. ወፍራሙ ልጅ ዛሬ ትምህርት ቤት አልመጣም።

3. መምህራችን ሰነፍ ተማሪ አይወዱም።
4. ረጅም ዱላ ይዞ ጥቁር ውሻ ያባርራል።
5. ብልህ ተማሪ ለፈተና ቀድሞ ይዘጋጃል።

## ክፍለጊዜ አስራስምንት

**ለ. ቀጥሎ የቀረቡትን ቅጽሎች በዓረፍተነገር ተጠቅማችሁ አሳዩ።**

**ለምሳሌ፡** አጭር፡ ሴና አጭር ቀሚስ መልበስ ትወዳለች።

1. ሆዳም
2. ቀበጥ
3. ብልጥ
4. ቀጭን
5. ቀይ
6. ቀዥቃዣ

# ምዕራፍ ስምንት

## ኤችአይቪ/ኤድስ

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የተማራችኋቸውን ውስብስብ የቀለም መዋቅር የተላበሱ ቃላት ቀስ በቀስ እያደገ በሚሄድ አፈፃፀም ፊደላቱን ጠብቃችሁ ትጽፋላችሁ፤
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን አስረጅ ፅሑፍ ታነባላችሁ፤ ቀጥሎ የራሳችሁን ሀሳብ ትፅፋላችሁ፤
- የድርሰት አላባዊያንን ትለያላችሁ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- ሳቢ እና ኢ-ሳቢ ግሶችን ትለያላችሁ፤
- ስነምዕላዳዊ ፍቺን ትለያላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት “ኤችአይቪ እና ኤድስ” በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረትም የቀረቡትን ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# ኤችአይቪ እና ኤድስ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ለሚከተሉት ቃላት በቃል ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ኤድስ          ለ. ኤችአይቪ

2. ከዚህ በፊት ስለኤችአይቪ/ኤድስ የምታውቁትን ተናገሩ።
3. ኤችአይቪ/ኤድስ በሰዎች ላይ የሚደርሰው ጉዳት ምንድን ነው?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ኤችኣይቪ እና በኤድስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. አንድ ሰው በበሽታው ተያዘ የሚባለው መቼ ነው?
2. በበሽታው የተያዙ ሰዎች እንዴት ጤናማ ኑሮ መኖር ይችላሉ?
3. “አንድ ሰው ኤችአይቪ አለበት ማለት ግን ይሞታል ማለት አይደለም።” የሚለው ሀሳብ ምንን ያመለክታል?
4. ያዳመጣችሁት ምንባብ ዋና መልዕክት ምንድንነው?

**ክፍለጊዜ ሦስት**

**ለ. ቀጥሎ የቀረቡት ዓረፍተነገሮች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት ምክንያት እያቀረባችሁ በጽሑፍ መልሱ።**

1. ኤችአይቪ እና ኤድስ በፍቺ ተመሳሳይ ናቸው።
2. ኤችአይቪ በሽታ ተከላካይ የሰውነት ክፍልን ይጎዳል።
3. አንድ ሰው ኤችአይቪ አለበት ማለት ይሞታል ማለት አይደለም።
4. ኤችአይቪ ያለባቸው ሰዎች እንደማንኛውም ጤነኛ ሰው ኑሯቸውን መምራት አይችሉም።

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክርክር ለማካሄድ የሚያስችላችሁ ማስታወሻና ተግባራት ቀርቦላችኋል። በመሆኑም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ትከራከራላችሁ።

**ማስታወሻ**

በክርክር ጊዜ ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

1. በሚቀርቡ መከራከሪያዎች ላይ በመረጃ የተደገፈ ዝግጅት ማድረግ፣
2. የሌላውን ተከራካሪ ሀሳብ አለማንቋሸሽ፣
3. ለተከራካሪ ሀሳብ ምክንያታዊ መልስ መስጠት፣ እና
4. ተራን ጠብቆ መናገር ናቸው።

**ተግባር አንድ**

1. በኤችአይቪ/ኤድስ የተጠቃን ሰው ማግለል ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ሀሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም በቡድን በመሆን ተከራከሩ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

2. የኤችአይቪ/ኤድስ ሥርጭትን በመቀነስ ረገድ ከጤና ተቋማት እና ከትምህርት ቤት የበለጠ አስተዋጽዖ ማድረግ ያለበት ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ሰዎችን በመጠየቅ አሳማኝ መረጃ እያቀረባችሁ በቡድን ተከፋፍላችሁ ተከራከሩ፡፡

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ክፍለጊዜ ስድስት**

በዚህ ትምህርት "ኤድስና መንስዔዎቹ" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሯቸው። ምንባቡንም ጥንድ ጥንድ በመሆን አንብቡ። ግልጽ ያልሆነላችሁ ሀሳብ ሲኖር ማንበባችሁን ቆም አድርጉና በማሰላሰል ሀሳቡን ለመረዳት ሞክሩ።

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ከዚህ በፊት ስለኤችአይቪ/ኤድስ የምታውቁትን ተናገሩ።
2. "ኤድስና መንስዔዎቹ" በሚል የቀረበው ምንባብ ምን መልዕክት የሚያስተላልፍ ይመስላችኋል?

## ኤድስና መንስዔዎቹ

ኤድስ የማይድን አደገኛ በሽታ ነው። የኤድስ መንስዔ ኤችአይቪ የሚባል ተሃዋስ ነው። ኤችአይቪ በረጅም ዓመታት ውስጥ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም ያዳክማል። በዚህም ሰውነት በቀላሉ ለብዙ በሽታዎች እንዲጋለጥ ያደርጋል።ስለሆነም በኤችአይቪ የተያዙ ሰዎች ህመማቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠና ይሄዳል። በሽታው ከሰው ወደሰው የሚተላለፈው በተለያዩ መንገዶች ነው። ለምሳሌ ስለታም ነገሮችን በጋራ መጠቀም እና ልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት መፈጸም ዋነኞቹ ናቸው።

በሽታው ከታወቀ ጊዜ ጀምሮ በበርካታ የዓለም ሀገራት ተዛምቶ የብዙዎችን ሕይወት ቀጥፏል። በኢትዮጵያም የብዙ ሰዎችን ሕይወት ከማጥፋቱም በላይ ዛሬም ድረስ እየተዛመተ ይገኛል። ምክንያቱም በሽታው ፈዋሽ መድኃኒት የሌለውና የሰዎችም አስተሳሰብ ባለመለወጡ የበሽታውን መዛመት መቀነስ አልተቻለም። በርግጥ በሽታው ፈዋሽ መድኃኒት ባይኖረውም የጸረ ኤችአይቪ መድኃኒት በመጠቀም ጉዳቱን መቀነስና ለረጅም ጊዜ አብረው ከበሽታው ጋር መቆየት ይቻላል። ይሁን እንጂ በበሽታው

የተጠቁ ሰዎች የጸረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት መውሰድን ከእምነት ጋር እያገናኙ ያቋርጣሉ። አንዳንድ የሃይማኖት አስተማሪዎችም መድኃኒት እንዳይጠቀሙ የሚገፋፉ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ።

## የንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች የተረዳችሁትን በቃል ተናገሩ።
2. እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች በመነሳት ቀጥሎ የሚመጣውን ሀሳብ ገምቱ።

ስለዚህ ይህንንም ችግር ለማስቀረት መንግሥት፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ኅብረተሰቡ፣ እና ግለሰብ ኋላፊነታቸውን በየደረጃው መወጣት አለባቸው። መንግሥት መዘናጋቱን ለማስቀረት ከሀይማኖት ተቋማት ጋር ምክክር ማድረግ አለበት። የሀይማኖት አባቶችም ለየእምነቱ ተከታዮች ተከታታይ ትምህርቶችን በመስጠት በመድኃኒቱ አጠቃቀም ላይ የሚታየውን ብዥታ ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል። ግለሰብም በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ ጥንቃቄዎችን ማድረግ አለበት። ከተያዙም መድኃኒቱን በመውሰድ ሕይወታቸውን ለማቆየት የራሳቸውን ኋላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የኤችአይቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ምንምን ናቸው?
2. ኤችአይቪ/ኤድስን መግታት ያልተቻለው ለምን ይመስላችኋል?
3. በኤችአይቪ/ኤድስ የተጠቁ ሰዎች መድኃኒቱን በአግባቡ የማይጠቀሙት በምን ምክንያት ነው?
4. የሰዎች አስተሳሰብ አለመለወጥ ኤችአይቪ/ኤድስን ከማሰራጨት አንጻር ያለው ጉዳት ምንድን ነው?
5. የጽሑፉ ዋና ሀሳብ አሳጥራችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።**

**ለምሳሌ፡** የተጠቁ፡ በበሽታው የተያዙ (በሽታው ያለባቸው)

በድህነት የተጠቁ ሀገራት ከድህነት ለመላቀቅ በርትተው መሥራት አለባቸው።

1. ማዳከም
2. ቀጥፏል
3. መቆየት
4. ማጥፋት
5. ጠና

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

በዚህ ትምህርት የድርሰት መጻፍ አላባውያንና የአስረጂ ጽሑፍ ምንነት የምትረዱበት ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም የቀረበውን ተግባር በትዕዛዙ መሠረት ትሠራላችሁ።

**ማስታወሻ**

ድርሰት በአንድ ርዕሰጉዳይ መነሻነት በተለያየ አንቀጽ ተከፋፍሎ የሚጻፍ ጽሑፍ ነው። ድርሰት ለመጻፍ በቅድሚያ መታወቅ የሚገባቸው መሠረታዊ አላባዊያን አሉ። እነዚህ አላባዊያንም በቅድመመጻፍ ጊዜና በመጻፍ ጊዜ የሚተገበሩ ናቸው።

**ሀ. የቅድመመጻፍ ጊዜ ተግባራት**

1. **ዓላማ፡** ድርሰት ለመጻፍ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የሚጻፍበትን ዓላማ ጠንቅቆ ማወቅ ነው።
2. **ርዕስ መምረጥ፡** ድርሰት ለመጻፍ የሚመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ጸሓፊውን ሊስበው፣ ሊያረካውና ሊያስደስተው ይገባል። ስለዚህ ተስማሚ ርዕስ መምረጥ የመጀመሪያው ተግባር ነው፡
3. **ርዕስን መወሰን (ማጥበብ)፡** የሚጻፍበት ርዕስ ዓላማውን የሚያሳካ መሆን አለበት። ስለዚህ የሚጻፈው ድርሰት በጊዜ፣ በቦታ፣ በቃላት መጠን፣ ወዘተ. የሚወሰን ነው። ስለሆነም ለዚህ ሁሉ በሚስማማ መልኩ ርዕሱን ማጥበብ ወይም መወሰን ያስፈልጋል።

4. **መረጃ ማፈላለግ፡** ቀደም ሲል የተገለጹት ተግባራት ከተከናወኑ በኋላ ቀጣዩ ሥራ ተገቢ መረጃ ማፈላለግና ማሰባሰብ ነው።
5. **ቢጋር መንደፍ፡** ወደዋናው ጽሑፍ ከመገባቱ በፊት አጠቃላይ የጽሑፉን አካሄድ የሚያሳይ ዝርዝር ወይም ንድፍ ነው።
6. **ተደራሲና አውድ፡** የጽሑፍ ዓላማ ታላሚ ከሚያደርገው አንባቢ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። ጸሐፊው ቁርጥ አድርጎ ለእነእገሌ ብሎ በገሃድ ባይወስንም ለእነማን እንደሚጽፍ ያውቃል። ስለዚህ ጸሓፊው እንደሚጽፍላቸው ተደራሲያን ከቋንቋ መረጣ ጀምሮ ሌሎችንም መርሆዎች መረዳት ይኖርበታል።

**ክፍለጊዜ አስር**

**ለ. የመጻፍ ጊዜ ተግባር**

1. ረቂቅ መጻፍ፡ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በርካታ ሀሳቦች ሊነሱ ይችላሉ። የረቂቅ ዋነኛ ግቡ የመጨረሻው ድርሰት ከማለቁ በፊት ማስተካከያና እርማት ለማድረግ ነው።

2. የመጨረሻ ረቂቅ መጻፍ፡ረቂቁ ተዘጋጅቶ ካበቃ በኋላ ያለአግባብ የገቡ ሀሳቦች ካሉ ይወገዳሉ። የፊደላት፣ የቃላት፣ የዓረፍተነገር፣ የሥርዓተነጥቦች፣ ወዘተ. ሙሉ ጥንቃቄ የሚደረግበት ተግባር ነው።

(ደረጀ ገብረ። 1996። ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት። (ገጽ 89-128 ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ)

**ክፍለጊዜ አስራአንድ**

**ተግባር ሁለት**

1. ከላይ በቀረበው የአስረጂ ጽሑፍ ምሳሌ መሠረት አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አስራሁለት**

2 የኤችአይቪ/ኤድስ የሚያስከትለውን ጉዳት አስረጂ እያቀረባችሁ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ (በማስታወሻው ላይ የተገነዘባችሁትን የአጻጻፍ ሂደት ተግብሩ::)

**ክፍለጊዜ አስራሦስት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ለመስጠት የሚያስችሏችሁ መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም መልመጃውን በትዕዛዙ መሠረት ትሠራላችሁ።

**መልመጃ ሦስት**

**ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።**

ለምሳሌ፡ ማጥበብ፡ ማስፋት

1. መዳከም በጋራ ብኸ ታ
2. መጋለጥ መዘናጋት

## ክፍለጊዜ አስራአራት

**ለ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ በትክክል አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ስኬት | ሀ. ማንኳሰስ |
| 2. ማትረፍ | ለ. ድካም |
| 3. ብርታት | ሐ. መመለስ |
| 4. ማሸነፍ | መ. መከልከል |
| 5. ማድነቅ | ሠ. መጥላት |
| 6. አንጋፋ | ረ. ማጣት |
| 7. መፍቀድ | ሰ. ጀማሪ |
| 8. መውደድ | ሸ. መረታት |
| 9. መውሰድ | ቀ. ውድቀት |

## ክፍለጊዜ አስራአምስት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ስለሳቢ እና ኢ-ሳቢ ግሶች ልዩነት እንዲሁም ስነምዕላዳዊ ፍቺ መስጠትን ትማራላችሁ። ስለሆነም የተሰጣችሁን ማስታወሻና ምሳሌዎች መነሻ በማድረግ መልመጃዎቹን በትዕዛዛቸው መሠረት ትሠራላችሁ።

### መልመጃ አራት

**ለምሳሌ፡**

ልጁ = ልጅ + -ኡ (እምር አመልካች)

ለበሰች = ለበስ- + -ኧች (መደብ አመልካች)

ለበሰ = ለበስ- + -ኧ (መደብ አመልካች)

ቤታችን = ቤት + -ኣችን (ባለቤትነት አመልካች)

**በምሳሌው መሠረት ድኅረአምድ ቅጥያ ምዕላዶቹ ያላቸውን ፍቺ በጽሑፍ ስጡ።**

1. በጎች
2. አጠበ
3. ልብሴ
4. ሰውዬው
5. ድስቱ
6. አበባዎች

## ክፍለጊዜ አስራስድስት

**ማስታወሻ**

ሳቢ ግስ የሚባለው ድርጊቱን ከባለቤት ወደተሳቢ የሚያሸጋግር ግስ ነው።

**ለምሳሌ፡** ጫልቱ ብርጭቆ ሰበረች።

በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ "ሰበረች" የሚለው ሳቢ ግስ ነው። ምክንያቱም ጫልቱ ድርጊቱን የፈጸመችው በራሷ ላይ ሳይሆን በብርጭቆው (ተሳቢ) ላይ ስለሆነ ነው።

ኢ-ሳቢ ግስ የሚባለው ደግሞ ድርጊቱ በራሱ በባለቤቱ ላይ ያለቀ ወይም ድርጊቱ ወደሌላ አካል የማይሻገር የግስ ዓይነት ነው። ለምሳሌ፡ አለሙ ተቀመጠ። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ "ተቀመጠ" የሚለው ኢ-ሳቢ ግስ ነው። ምክንያቱም የመቀመጡን ድርጊት የፈጸመው በሌላ አካል ሳይሆን በራሱ ላይ ስለሆነ ነው።

**ክፍለጊዜ አስራሰባት**

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ኢ-ሳቢ እና ሳቢ ግሶችን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡**

1. ለሚ ዛፍ ቆረጠ፡፡
2. አልማዝ ገበያ ሄደች፡፡
3. ካሳሁን ልብሱን ቀደደ፡፡
4. ፋጡማ ፈተና ስላለፈች ተደሰተች፡፡
5. ለሊሴ መስኮቱን ከፈተች፡፡

**ክፍለጊዜ አስራስምንት**

**ለ. ኢ-ሳቢ እና ሳቢ ግሶችን በመጠቀም የራሳችሁን ዓረፍተነገር መሥርቱ፡፡**

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልማዳዊ ተግባራት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የሚነበብላችሁን ታሪክ ታዳምጣላችሁ፤
- በአስተያየቶች ላይ መስማማት አለመስማማታችሁን ትገልጻላችሁ፤
- ቀለል ያለና አጭር ታሪክን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ወደ ሰንጠረዥ ታሸጋግራላችሁ፤
- ካነበባችሁት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር ትመሠርታላችሁ።

ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት "የአበራሽ ታሪክ" በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# የአበራሽ ታሪክ



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።**

1. ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላትና ሀረጋት በቃል ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ቃሬዛ

   ለ. የቤተሰብ ዕቅድ

   ሐ. የልምድ አዋላጅ

2. ከዚህ በፊት በአካባቢያችሁ ልጆችን አከታትለው በመውለድ ችግር የደረሰባቸውን እናቶች ታውቃላችሁ? ምን ዓይነት ጉዳት እንደደረሰባቸው ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

3. በአከባቢያችሁ ከባህላዊ ልማድ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ተግባራትን ተናገሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አበራሽ የምትኖረው የት ነው?

2. በምታዳምጡበት ጊዜ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ መዝግቡ፤ ያልተረዳችኋቸው እንግዳ ቃላት ካጋጠሟችሁም ለይታችሁ ጻፉና ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. አበራሽ ስንት ልጆች አሏት?
2. አበራሽ የመጀመሪያ ልጇን ያረገዘችበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. አበራሽ አራተኛ ልጇን ስታረግዝ ከወትሮው የተለየ የጤና እክል የገጠማት ለምን ይመስላችኋል?
4. የአበራሽ ቤተሰቦች በወቅቱ አበራሽን ወደሕክምና ለማድረስ ያመነቱት ለምን ይመስላችኋል?
5. በልምድ አዋላጅና በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ መካከል ያለውን ልዩነት ተናገሩ።
6. ከአበራሽ ሕይወት የተማራችሁት ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

**ክፍለጊዜ ሦስት**

**ለ. "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት ምክንያት እያቀረባችሁ በጽሑፍ መልሱ።**

1. የአበራሽ ልጆች ያላቸው የዕድሜ ልዩነት ተመሳሳይ ነው።

2. አበራሽ የመጀመሪያ ልጇን ያረገዘችው እናት ለመሆን በነበራት ጉጉት ብቻ ነው።
3. አበራሽ ስለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ጥሩ ግንዛቤ ነበራት።
4. አበራሽ አራተኛ ልጇን ስታረግዝ የቅድመወሊድ ክትትል ማድረግ ጀመረች።
5. አበራሽን ወደጤና ጣብያ ወስዶ ለማሳከም ቤተሰቦቿ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው።

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ንግግር ለማድረግ የሚያስችሏችሁ ተግባራት ቀርቦላችኋል። በመሆኑም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ንግግር ታደርጋላችሁ።

**ተግባር አንድ**

1. በአበራሽ ታሪክ ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ክስተቶች ምንምን እንደሆኑ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

3. በአበራሽ ላይ የደረሰው ነገር በሌሎች እናቶች ላይ እንዳይከሰት ከባለታሪኳ፣ ከቤተሰብ፣ ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና ከኅብረተሰቡ፣ ከመንግሥት ምን እንደሚጠበቅ በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "ያለዕድሜ ጋብቻ" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሯቸው። ስታነቡም የምንባቡን ሀሳብ እየተረዳችሁ በየግላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?
2. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ልማዳዊ ተግባራት በመዘርዘር ተናገሩ።

# ያለዕድሜ ጋብቻ

በኢትዮጵያ የፌደራል ሕግ ለትዳር የሚያበቃው ዕድሜ 18 ዓመት መሆኑን ይደነግጋል። ከ18 ዓመት በፊት የሚፈጸም ጋብቻ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ነው። ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመፈጸም የሚደግፉ ምክንያቶች ርስበርሳቸው የተያያዙና አንዱ ሌላኛውን የሚያጠናክሩ ናቸው። ከነዚህም መካከል ኢኮኖሚያዊ ችግር በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች አንዱ ነው። ቤተሰቦች ለልጃቸው የትዳር ጓደኛ የሚፈልጉት ከነሱ ተመጣጣኝ ወይም በተሻለ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ካሉ ቤተሰቦች ነው። ብዙ ቤተሰቦች ዝምድናን ለማጠናከር ሲሉም ልጃቸውን በልጅነቷ ይድራሉ። በተጨማሪም ወላጆች ከመሞታቸው በፊት የልጅልጅ ማየትና ዘራቸው መቀጠሉን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ። ወላጆች ሀብት እያለ በጊዜ ደግሰው አለማቸውን ማየትም ይሻሉ።

እንዲሁም ማህበራዊና ባህላዊ ምክንያቶች ያለዕድሜ ጋብቻ እንዲፈጸም የጎላ ሚና ይጫወታሉ። ወላጆች ለልጆቻቸው በሌሎች የጋብቻ ጥያቄ ሲመጣ ከፍተኛ ደስታና ኩራት ይሰማቸዋል። ጠለፋንም በመፍራት ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ያለዕድሜያቸው ለመዳር ይገደዳሉ።

በዕድሜ የገፉ ሰዎችም በኤችአይቪ መያዝን በመፍራት ድንግል የሆኑ ወጣት ልጃገረዶችን ማግባት ይፈልጋሉ። ያለ ዕድሜ ጋብቻ ሴቷ ለባሏ የምትገዛ እንድትሆን ለማድረግም ሲባል ይከናወናል።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ያለዕድሜ ጋብቻ የሚባለው ከስንት ዓመት በፊት የሚፈጸም ነው?
2. ያላዕድሜ ጋብቻ የሚከሰትባቸው ምክንያቶች ምንምን ናቸው?

በወጣትነታቸው ያገቡ ሴት ልጆች በአካል፣ በስነልቦና፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስክ ብዙ ጉዳቶች ያጋጥሟቸዋል። ያለዕድሜ ጋብቻ ያለዕድሜ በማርገዝ በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት ለሞትና ለተዛማጅ የጤና ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ያጋልጣል። ታዳጊ ልጃገረዶች በዳሌያቸው አጥንት ትንሽነት ምክንያት ለተሰናከለ ምጥ እና በወሊድ ምክንያት ለሚመጣ የፌስቱላ ችግር በከፍተኛ ደረጃ ይጋለጣሉ። በዚህም ኢትዮጵያ በወሊድ ምክንያት ፌስቱላ በብዛት ከሚከሰትባቸው ሀገራት አንዷ ናት። ፌስቱላ ያለባት ሴት ሽንቷንና ሰገራዋን መቆጣጠር ስለማትችል በአካሏ፣ በማኅበራዊና ሥነልቦናዊ ጤናዋ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። እንዲህ ያለ ችግር ያለባቸውን ብዙዎቹን ሴቶች ባሎቻቸው ይፈቷቸዋል። ያለዕድሜያቸው ያገቡ ልጃገረዶች በስነ አካላዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች በግብረሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጡ ናቸው።

ያለዕድሜ ጋብቻ ጉዳቶች መካከል የወጣትነት ጊዜን ማጣት፣ ነጻነትንና ዕድገትን መነፈግ፣ ከፍተኛ የሆኑ ማኅበራዊ፣ ሥነልቦናዊ እና የስሜት ጉዳት ማስከተል ይጠቀሳሉ። ያለዕድሜያቸው ያገቡ

ወጣት ሴቶች ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብታቸውን ያጣሉ። በቤት ውስጥ ብቻ ሊወሰኑና የቤት እመቤት ሆነው ሊቀሩ ይችላሉ። ራሳቸውን የሚያሳድጉባቸውና ማንነታቸውን የሚያጎለብቱባቸውን ዕድሎች ያጣሉ። ያለዕድሜ ጋብቻ የመማር ዕድላቸውን ይነፍጋል። ይህም የራሳቸውን ዕድገት ከመወሰኑ ባሻገር በራሳቸውና በልጆቻቸው ሕይወት ላይ ዘላቂ ጉዳት ትቶ ያልፋል። ብዙዎቹ ያለዕድሜያቸው ያገቡ ልጃገረዶች የመደህየት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት ወደከተማ በመኮብለል አብዛኞቹ ለመኖር ሲሉ ሴትኛ አዳሪ ይሆናሉ።

ያለዕድሜ ጋብቻ ሰብዓዊ መብቶችንም የሚጥስ ነው። ያለዕድሜ ጋብቻ በቤተሰብና በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ደህንነት ላይ የሚያደርሰው ጉዳትም አለ። ልጃገረዶች ሳይማሩ ሲቀሩ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ዝግጅት ስለሚጎድላቸው በየደረጃው ቤተሰብንና በአጠቃላይ ሀገርን ይጎዳል።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ያለዕድሜ ጋብቻ ጎጂ የሚሆነው እንዴት ነው?
2. “ያለዕድሜ ጋብቻ ሴቷ ለባሏ የምትገዛ እንድትሆን ለማድረግም ሲባል ይከናወናል።” የሚለው ሀሳብ ምን ለማለት ነው?

3. ያለዕድሜያቸው ያገቡ ልጃገረዶች ምን ዓይነት የጤና እክል ይገጥማቸዋል?
4. ልጃገረዶች ሳይማሩ ሲቀሩ በየደረጃው በቤተሰብና በሀገር ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምን ይመስላችኋል?
5. የጽሑፉን ዋና መልዕክት ግለጹ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

**ለ. ባነበባችሁት ምንባብ መሠረት ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ በመጠቀም ያለዕድሜ ጋብቻ የሚፈጸምባቸውን ዋናዋና ምክንያቶችና የሚያስከትላቸውን ዋናዋና ጉዳቶች ዘርዝሩ።**

| | |
|---|---|
| **ያለዕድሜ ጋብቻ**<br>የሚፈጸምበት ምክንያቶች | ለምሳሌ፡-የኢኮኖሚ ችግር<br>__________<br>__________<br>__________<br>__________ |
| **ያለዕድሜ ጋብቻ**<br>የሚያስከትላቸው ጉዳቶች | ለምሳሌ፡-የጤና እክል<br>__________<br>__________<br>__________<br>__________ |

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

**ሐ. በቡድን በመወያየት ያለዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል ከሚከተሉት ባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ በቀረበላችሁ ሠንጠረዥ ውስጥ ሙሉ።**

| ተ.ቁ | ማኅበረሰብ | ወላጅ | መንግሥት |
|---|---|---|---|
| 1 | ምሳሌ፡ ያለዕድሜ ጋብቻን እንደባህል አለመቀበል | | |
| 2. | | | |
| 3. | | | |
| 4. | | | |

## ክፍለጊዜ አስር

መ. የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ ባሉ ባዶ ቦታ በማስገባት አውዳዊ ፍቺአቸውን አሳዩ።

ይጫወታል ታዳጊ ማንነት ይፈጥራል

መከብለል ተዛማጅ የሚተላለፍ

1. ያለዕድሜ ጋብቻ ስለሚፈጥረው ችግር ለ ________ ሕጻናት ማስተማር አስፈላጊ ነው።
2. የኢኮኖሚ ችግር ያለዕድሜ ጋብቻ እንዲፈጸም ከፍተኛ ሚና ________ ።
3. በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ዜጎች ድህነትን ለመሸሽ ወደአውሮፓ ሀገራት ________ ይመርጣሉ።
4. ኮቪድ-19 በትንፋሽ አማካኝነት ________ በሽታ ነው።
5. በወሊድ ጊዜ እክል የገጠማቸው እናቶች ለሌሎች ________ ችግሮች ይጋለጣሉ።

ክፍለጊዜ አስራአንድ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት የማመልከቻ ደብዳቤ ለመጻፍ የሚያስችላችሁ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም የቀረቡትን ተግባራት በትዕዛዞቻቸው መሠረት ሥሯቸው።

### ማስታወሻ

የማመልከቻ ደብዳቤ ለልዩ ልዩ ተግባራት ይጻፋል። ለምሳሌ ሥራ ለመቀጠር፣ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ፍቃድ ለመጠየቅ፣ ድጋፍ ለማግኘት ወዘተ። የማመልከቻ ደብዳቤ ርዝመቱ አጭር መሆን አለበት። ከአንድ ገጽ መብለጥ የለበትም። የማመልከቻ ደብዳቤ እንደየዓላማው በውስጡ ሊይዛቸው የሚገቡ ይዘቶች አሉ። ለምሳሌ የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ የግል መረጃ፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድና ግላዊ አስተያየቶችን ያካትታል። የግል መረጃ የሚባለው ስም እና አድራሻዎችን (ለምሳሌ፡- ስልክ ቁጥር፣ ኢሜይል) ያካትታል።

የሥራ ማመልከቻ ሦስት ክፍሎች ይኖሩታል። አንደኛው መግቢያ አንቀጽ ሲሆን አንቀጹ እውነታን መሠረት አድርገን ጥንካሬያችንን የምንገልጽበት ነው። የሥራ ደረጃችንንና ፍላጎታችንንም እንዲሁም ያመለከትንበት መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ካለው የት ቢመድቡን እንደሚሻል እንገልጽበታለን።

ሁለተኛው ክፍል የደብዳቤው ዋና አካል ነው። በክፍሉ የሰለጠንበትን የሙያ መስክና የስራ ልምዳችንን እንገልጻለን። የስራ ልምዳችን ለስራ ያለንን ብቃት የሚያረጋግጥ መሆኑን ማሳወቅ ያስፈልጋል።

ሦስተኛው መዝጊያ ክፍል ሲሆን ተጨማሪ ችሎታዎች ካሉን የምንገልጽበት ክፍል ነው። ለምሳሌ ኮምፒዩተር የምንችል ከሆነ እንገልፃለን። ቀጣሪውን የሚያራሩ ቃላትን በመጠቀምም እንጽፋለን።

**ክፍለጊዜ አስራሁለት**

***ምሳሌ፡***

*ናናቲ ወዬሣ፣*
*ፖ.ሣ.ቁ. 123456*
*nanatiwayessa@email.com*
*ሐምሌ 30, 2013.*
**ነቀምቴ**

**ለነቀምቴ መምህራን ኮሌጅ**

በ20/11/2013 ዓ.ም ኮሌጃችሁ የሰው ኃይል አማካሪ ለመቅጠር ማስታወቂያ ማውጣቱ ይታወቃል። ስለሆነም በዚህ ቦታ ላይ ለመቀጠር የሚያስችለኝ የተሻለ ልምድና በቂ ዕውቀት አለኝ።

ላለፉት አምስት ዓመታትም በዚሁ ሙያ ላይ ተሠማርቼ ከፍተኛ የሙያ ብቃት ግምገማ ውጤት አስመዝግቤ የምስክር ወረቀት

ተሰጥቶኛል። በመሆኑም መስፈርቱን የማሟላ ከሆነ መስሪያ ቤታችሁ ቢቀጥረኝ በቁርጠኝነትና በታማኝነት ለመሥራት ጽኑ ፍላጎት ያለኝ መሆኑን በትህትና እገልጻለሁ።

ከሚፈለገው የሥራው መስፈርት በተጨማሪም የኮምፒውተር መሠረታዊ ክሂሎትና የጸረ ሙስና ስልጠናዎችን በመውሰዴ ለመሥሪያቤቱ የተሻለ አስተዋጽዖ ለማበርከት ያስችለኛል ብዬ አምናለሁ።

ከሠላምታ ጋር!
*ናናቲ ወዬሣ*
ፊርማ

## ክፍለጊዜ አስራሦስት

**ተግባር ሁለት**

1. ከላይ በቀረበው የሥራ ማመልከቻ ምሳሌ መሠረት የግላችሁን አንድ የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

## ክፍለጊዜ አስራአራት

2. በትምህርት ሦስት "ያለዕድሜ ጋብቻ" ከሚለው ምንባብ ጋር ተያያዥነት ያለው የራሳችሁን አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

## ክፍለጊዜ አስራአምስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ቃላትን በተቃራኒ ፍቺያቸው ማዛመድ የምትለማመዱበት መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም መልመጃውን በትዕዛዙ መሠረት ሥሩ።

### መልመጃ ሦስት

በ"ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩ ቃላት ትክክለኛ ተቃራኒያቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ታላላቅ | ሀ. ወጥተው |
| 2. መሰደድ | ለ. መያዝ |
| 3. ማመን | ሐ. መካድ |
| 4. ተፈጥሯዊ | መ. ቆሻሻ |
| 5. ማምለጥ | ሠ. አስቀያሚ |
| 6. ማራኪ | ረ. ታናናሽ |
| 7. ንፁህ | ሰ. መመለስ |
| 8. ወርደው | ሸ. ሰው ሠራሽ |

## ክፍለጊዜ አስራስድስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መመሥረትን ትማራላችሁ። ስለሆነም የተሰጣችሁን ምሳሌዎች መነሻ በማድረግ መልመጃውን በትዕዛዛቸው መሠረት ሥሩ።

**ሀ. የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።**

ምሳሌ፡ ወይዘሮ ሮሚ ለልጃቸው አዲስ ልብስ ገዝተዋል። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ "ገዝተዋል" የሚለው ግስ ዓረፍተነገሩ በሃላፊ ጊዜ መነገሩን ያሳያል።

## ክፍለጊዜ አስራሰባት

**ለ. ቀጥሎ ከቀረቡላችሁዓረፍተነገሮች ሃላፊ ጊዜ አመልካች ግሶችን የተጠቀሙት የትኞቹ እንደሆኑ ለይታችሁ አሳዩ።**

1. በአንድ የገጠር ሠርግ ሥነሥርዓት ላይ ታድሜያለሁ።
2. የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ እየተማሩ ነው።
3. ልጅቷ አንገቷ ላይ ጌጣጌጦችን አድርጋለች።
4. የክፍላችን ተማሪ በተደጋጋሚ ከክፍል ይቀራል።
5. ያለዕድሜ ጋብቻ ሰብዓዊ መብቶችን የሚጥስ ነው።
6. እሱ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል።
7. ዛሬ ወደገበያ ለመሄድ ዕቅድ አለኝ።
8. እሷ ጠንክራ በመሥራቷ ጥሩ ውጤት አስመዘገበች።
9. እሱ ወደቤቱ እየተመለሰ ነው።
10. የዛሬው ስብሰባ ቶሎ ተጠናቀቀ።

## ክፍለጊዜ አስራስምንት

**ሐ. የሃላፊ ጊዜን ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ በመጻፍ ለክፍሉ ተማሪዎች አንብቡ።**

# ምዕራፍ አሥር

# ሴቶችን ማብቃት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ፍላጎቶቻችሁን ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ትገልጻላችሁ፤
- ግለ ታሪክ ትጽፋላችሁ፤
- ተገቢ የአነባበብ ስልትን በመከተል ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ምንባብ ታነባላችሁ፤
- ቃላትን በምዕላድ ከፋፍላችሁ ታሳያላችሁ፤
- በዓረፍተነገሮች ውስጥ ቀጥተኛ (ርቱዕ) እና ቀጥተኛ ያልሆኑ (ኢ-ርቱዕ) ተሳቢዎችን ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት “የሴቶች እኩልነት” በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ታዳምጣላችሁ። ባዳመጣችሁት መሠረትም የቀረቡትን ጥያቄዎች ትሠራላችሁ።

# የሴቶች እኩልነት

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በቃል ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ሥርዓተጾታ
   ሐ. የጾታ እኩልነት
   ለ. ብሂል

2. “የሴቶች እኩልነት” የሚለው ምንባብ መልዕክቱ ስለምን ይመስላችኋል?
3. ከዚህ በፊት ስለሴቶች እኩልነት የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ጾታ ሳይለይ ሁሉም ሕፃናት እኩል የመማር መብት እንዳላቸው የተደነገገው መቼ ነው?
2. “የሥርዓተጾታ እኩልነትን ማረጋገጥ” ሲል ምን ማለት ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች    ክፍለጊዜ ሁለት

### መልመጃ አንድ

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. “ሴቶች ለእነሱ ብቻ ባልተሰጡ የቤት ውስጥ ሥራዎች ይጠመዳሉ።” ሲባል ምን ለማለት ነው?

2. በሴቶች ላይ ለረጅም ጊዜ ሥር የሰደደው የተሳሳተ ማህበራዊ አመለካከት ምንድን ነው?
3. በአሁኑ ሰዓት ሴቶችን ለማበረታታት ምንምን ተግባራት እየተከናወኑ ነው?
4. “ሴት ወደማጀት ወንድ ወደችሎት” የሚለው አባባል ምንን ይገልጻል? በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት ያለው ይመስላችኋል? ለምን?
5. ከትምህርት ቤት ባሻገር የሴቶች ተሳትፎ በምን በምን መስክ ሊረጋገጥ ይገባል ትላላችሁ?

**ክፍለጊዜ ሦስት**

**ለ. ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በትክክል አሟሉ።**

| ዓመተምህረት | ድንጋጌዎች |
|---|---|
| ለምሳሌ፡1981 | ሴቶች ከወንዶች እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ተደነገገ። |
| 1990 | |
| 1995 | |
| 2005 | |

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት አዳምጦ ጽብረቃ ለማካሄድ የሚያስችላችሁ ተግባራት ቀርበውላችኋል። በመሆኑም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ንግግር ታደርጋላችሁ።

**ተግባርአንድ**

1. ካዳመጣችሁት ምንባብ የተረዳችሁትን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

2. የሴቶች እኩልነትን ለማረጋገጥ ሊሠሩ የሚገባቸውን ጉዳዮች ሰዎች በመጠየቅና በማንበብ ያገኛችሁትን መረጃ በክፍል ውስጥ በንግግር አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "ሴቶችን ማስተማር" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በቅድመንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረንባብ ጊዜ የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሯቸው። ምንባቡን ስታነቡ የማታውቋቸውን ቃላትና ሐረጋት እየጻፋችሁና ሀሳቡን እየተረዳችሁ በየግላችሁ በለሆሰስ አንብቡ።

### ቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ሴቶችን የማስተማር ጠቀሜታው ምንድን ነው?
2. በኢትዮጵያ ውስጥ በትምህርት ዘርፍ መልካም አርዓያ ከሆኑ ሴቶች መካከል የምታውቋቸውን ጥቀሱ።
3. በአርዓያነት የተጠቀሱበትን አንኳር ምክንያቶች ተናገሩ።

# ሴቶችን ማስተማር

ከጥቂት አስርት ዓመታት በፊት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ሴቶችን ማስተማር የተለመደ አልነበረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደዋል። በዚህ የተነሳ የወንዶችን ያህል የመማር ዕድል ባያገኙም የትምህርት ተሳትፏቸው ግን ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል።

ሴቶች ከወንዶች እኩል የመማር መብታቸው ከተረጋገጠላቸው በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊና መስኮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ሴቶች የትምህርት ዕድል ካገኙ ቅድሚያ ራሳቸውን ተጠቃሚ ያደርጋሉ፤ በጥሩ ክፍያ ይቀጠራሉ፤ ወይም የተለያዩ ሥራዎችን ፈጥረው ገቢያቸውን ከፍ ያደርጋሉ። ገቢያቸውን ስለሚያሳድጉ ከወጪ ጋር በተያያዘ በቤት ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን በቀላሉ ያስወግዳሉ። ቤተሰባዊ ሰላምንም ያሰፍናሉ።

ሴቶችን በትምህርት ማብቃት የውልደት መጠንንም ለመቀነስ ያስችላል። የተማሩ ሴቶች ስለቤተሰብ ምጣኔ ያላቸው ግንዛቤ ካልተማሩ ሴቶች የተሻለ ስለሆነ መጥነው ይወልዳሉ። ሴቶች ወደትምህርት ቤት ከተላኩ በለጋ ዕድሜያቸው ባል የማግባት ዕድላቸው ይቀንሳል። ይህም በዝቅተኛ ዕድሜያቸው የማርገዝና የመውለድ አጋጣሚውን ይቀንስላቸዋል።

በኢትዮጵያ እ.አ.አ. ከ2011-2013 ድረስ 20 በመቶ የሚሆኑ ልጃገረዶች 18 ዓመት ሳይሞላቸው ሊያረግዙ እንደሚችሉ ጥናቶች አረጋግጠዋል። በመሆኑም ሴቶችን ወደትምህርት ቤት በመላክ የእርግዝና ጊዜያቸውን ማዘግየትና የውልደት መጠንንም መቀነስ ይቻላል። በሌላም በኩል ሴቶች ከተማሩ እስከሁለት ዓመት ሕፃናትን በአግባቡ ጡት ማጥባት እንዳለባቸው ይገነዘባሉ። ይህን ለማድረግም አከታትለው ከመውለድ ይቆጠባሉ። የሚወልዷቸውንም ሕፃናት ቁጥር ከገቢያቸው ጋር ያመጣጥናሉ፤ ተገቢ እንክብካቤም ያደርጋሉ።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች የተረዳችሁትን በቃል ተናገሩ።
2. ቀጥሎ የሚመጣውን ሀሳብ ገምቱ።

ሴቶችን በማስተማር የሕፃናትን ሞት መቀነስም ይቻላል። ሴቶች ከአረገዙበት ዕለት ጀምሮ ሕፃናትን ጡት አጥብተው እስከሚያሳድጉ ድረስ የህክምና ክትትል ያስፈልጋቸዋል። ይህን ማድረግ የሚችሉት ደግሞ ሲማሩ ነው። ስለሆነም ሴቶች ከተማሩ የት መውለድ፣ እንዴት ማሳደግና መንከባከብ እንደሚችሉ ያውቃሉ፤ ተግባራዊ ለማድረግም ይጥራሉ።ሴቶች ጡት በማጥባት ሂደት ከጨቅላ ሕፃናት ጋር ሰፊ ጊዜ ሊያሳልፉ ይችላሉ። ስለሆነም ሕፃናትን ከበሽታ ለመከላከልና ህይወታቸውን ከሞት ለመታደግ ሴቶችን ማስተማር ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው። ከተማሩ

እናቶች የተወለዱ ሕፃናት በህይወት የመኖር ዕድላቸው ካልተማሩ እናቶች ከተወለዱ ሕፃናት ከእጥፍ በላይ እንደሆነም ጥናቶች ያሳያሉ።

ሴቶችን ከወንዶች እኩል እንዲማሩ በማድረግ በአጭር ጊዜ ሀገራዊ ዕድገት ማምጣት ይቻላል። ከአንድ ሀገር ህዝብ ግማሽ ያህሉን ቁጥር የሚሸፍኑት ሴቶች ናቸው። ስለሆነም ሴቶች ከመሠረታዊ ትምህርት እስከከፍተኛ ትምህርት ደረጃ እንዲማሩ ከተደረገ በሀገራዊ ፖሊሲዎችና በተለያዩ የልማት መስኮች ላይ በንቃት ይሳተፋሉ። ሀገራት ለሚነድፏቸው ግቦች ስኬታማነት የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው። ሴቶች ይህን ሚና ሊያከናውኑ የሚችሉት ደግሞ በቂ ትምህርት ሲያገኙ ነው።

ሴቶች በፖለቲካዊና በማህበራዊ ዘርፎች ንቁ ተሳታፊና ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆን የሚችሉት ሲማሩ ነው። የአመራርነትን ሚና በአግባቡ ለመወጣት ትምህርት አስፈላጊ ነው። ሴቶች እንደወንዶች የመማር ዕድል ካገኙ ጥሩ መሪዎች ይሆናሉ። በዓለማችን የመማር እድል ያገኙ ሴቶች ብቁ የሀገር መሪ እንደሚሆኑ መጠራጠር አይቻልም። ለዚህም በዓለማቀፍ ደረጃ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ በርካታ ሴቶች ምስክር ናቸው። ሴቶች ከተማሩ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተናግረው የሚያሳምኑና የሀገራቸውን በጎ ገጽታ የሚያሳዩ ይሆናሉ። ለሀገር የሚጠቅሙ

አዳዲስ አሰራሮችን ያፈልቃሉ። የተማሩ ሴቶች በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችም ላይ ተሳትፏቸው ይጨምራል።

በአጠቃላይ በትምህርት ዘርፍ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት መረጋገጡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። ሴቶች ሲማሩ የተሻለ ገቢ ያገኛሉ። የውልደት መጠንንና የሕፃናትን ሞት ይቀንሳሉ። ሀገራቸውን ማሳደግና ሀገራዊ ግቦችን ማሳካት ይችላሉ። በፖለቲካውም ዘርፍ ንቁ ተሳታፊና ተፅዕኖ ፈጣሪ ይሆናሉ። በተለያዩ የአመራርነት ቦታዎች ላይ በብቃት ይሳተፋሉ። ስለሆነም ሴቶችን በትምህርት ማብቃት ለነገ የሚባል ተግባር ሊሆን አይገባም።

(ሲዳ። 2010።ኢዱኬሽንጀንደርኢኳሊቲ፤ለውጥተደርጎበትየተወሰደ)

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. “የተማሩ ሴቶች ካልተማሩ ሴቶች ይልቅ ቤተሰባዊ ሰላምን ያሰፍናሉ” በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? እንዴት?
2. የተማሩ ሴቶች በዕቅድ ለመውለድ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምንምን ናቸው?
3. በሥርዓተጾታ ክበብ ውስጥ ምንምን ተግባራትን ይፈጸማሉ?

4. ከጥቂት ዓመታት በፊት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ሴቶችን ማስተማር ትኩረት ያልተሰጠው ለምን ይመስላችኋል?
5. የሴቶችና የወንዶች የትምህርት ተሳትፎ እንዲመጣጠን ምን መደረግ ያለበት ይመስላችኋል?
6. በንባብ ጊዜ የመዘገባችኋቸውን ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍቺ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

**ለ. የተማሩና ያልተማሩ ሴቶች የሚመሳሰሉባቸውንና የሚለያዩባቸውን ባህርያት በሠንጠረዡ ውስጥ ግለጹ።**

| ተ.ቁ | ተመሳስሎ | ልዩነት | |
|---|---|---|---|
| | | የተማሩ ሴቶች | ያልተማሩ ሴቶች |
| 1 | ምሳሌ፡ ተፈጥሯዊ የሴትነት ባህርይ | የቤተሰብ ምጣኔ ግንዛቤ አላቸው | ግንዛቤ የላቸውም። |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

**ሐ. ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺአቸውን ስጡ። በቃላቱም ዓረፍተነገር መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**ለምሳሌ፡** ፈጣሪ - የሚያመጡ፣ የሚያስከትሉ
ያለዕድሜ ጋብቻ ችግር ፈጣሪ የባህላችን ክፍል ነው።

1. መረጋገጡ
2. ለመወጣት
3. ምጣኔ
4. ያፈልቃሉ
5. ጨቅላ

**ክፍለጊዜ አስር**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ግለታሪክ መጻፍን የሚያለማምዳችሁ ተግባር ቀርቦላችኋል። ስለሆነም የቀረበውን ተግባር በትዕዛዙ መሠረት ትሠራላችሁ።

**ማስታወሻ**

ግለታሪክ ማለት የራስን የሕይወት ልምድ ከውልደት ጀምሮ በሕይወት እስካለ ድረስ የሚተርክ ኢ-ልቦለዳዊ ጽሑፍ ነው። ጽሑፉ በራሱ በባለቤቱ የሚጻፍ ነው። በውስጡ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል።

- ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቦታና ጊዜ የወላጆች ሙሉ ስም፣
- የአስተዳደግ ሁኔታ፣
- የትምህርትቤት ህይወት የተገኙ ሽልማቶችና ምስጋናዎች፣
- የወደፊት ራዕይ፣
- ልምዶች፣ እና የመሳሰሉት።

**ለምሳሌ**

ስሜ ለሚ ይባላል። የተወለድኩት ከእናቴ ወይዘሮ አለሚቱ ጋዲሣ እና ከአባቴ አመንሲሳ ሁንዴሳ በ1988 ዓ.ም. በአምቦ ከተማ ነው።

የልጅነት ጊዜዬን ብዙም አላስታውስም። ግን በጣም ንቁ እና ተግባቢ ልጅ እንደነበርኩ እናቴ ነግራኛለች። መልሶችን ሳልጠብቅ በየደቂቃው በደርዘን የሚቆጠሩ ጥያቄዎችን እጠይቃለሁ። ወላጆቼ መጽሐፍት እና ትምህርታዊ ፊልሞችን በልጅነቴ ያቀርቡልኝ የነበረውም ለዚህ ይመስለኛል።

ዕድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ አባቴ ወደትምህርት ቤት ወሰደኝ። በትምህርት ቤት ሳለሁ ለታሪክ እና ለሳይንስ ጥልቅ ፍቅር ነበረኝ። በመሆኑም በታሪክ እና በሳይንስ ትምህርት ጥልቅ ዕውቀት አግኝቻለሁ። ዛሬ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት የአራተኛ ዓመት ተማሪ ነኝ። በዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያ ዓመት ትምህርቴ የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ ተሸልሜያለሁ።

የትምህርት ወጪዎቼንም ለመሸፈን ከትምህርቴ ጎን ለጎን ሌሎች ተማሪዎችን በማስጠናት መጠነኛ ገንዘብ ለማግኘት እሠራለሁ። በዚህም የትርፍ ሰዓት ሥራን እና የሙሉ ጊዜ ትምህርትን አጣምሬያለሁ። በዚህ ሂደት ሕይወት አልጋ በአልጋ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ። ተግዳሮቶች እና ችግሮች የህይወት ዋና አካል ናቸው።

ስለሆነም ካሳለፍኩት የሕይወቴ ውጣውረዶች ሁለት ዋናዋና ምክንያቶች ስኬትን እንደሚወስኑ ተምሬያለሁ። የመጀመሪያው ቆራጥነት ሲሆን ሁለተኛው ስኬታማ የመሆን ፍላጎት ነው። ልክ

እንደሥራ እና ማጥናት ያሉ ግብዎን ለማሳካት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል። ከውድቀት በኋላ ለማገገም እና እንደገና ወደ ግብዎ ለመድረስ ጠንካራ ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሌለ ስኬታማ መሆን ፈጽሞ አይቻልም። ስኬት ድክመቶችን ማወቅ እና በእውነት ሊረዱዎት ከሚፈልጉ ሰዎች ድጋፍን መቀበል ነው። ለምሳሌ ለትምህርት ጥረቶቼ ወላጆቼ ድጋፍ ባይሰጡኝ ዛሬ በሕግ ትምህርት ቤት አልገኝም ነበር።

**ክፍለጊዜ አስራአንድ**

**ተግባር ሁለት**

1. ከላይ የተሰጠውን ማስታወሻ መሠረታዊ ሀሳቦች በመጠቀም የየራሳችሁን ግለታሪክ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

**ክፍለጊዜ አስራሁለት**

2. በተግባር ሁለት ትዕዛዝ “1” ሥር የጻፋችሁትን ግለታሪክ ለጓደኛችሁ በመስጠት ተራረሙ፡፡

**ክፍለጊዜ አስራሦስት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል የሚያስችላችሁ መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም መልመጃውን በትዕዛዞቹ መሠረት ሥሩ።

**መልመጃ ሦስት**

**ሀ.ቀጥሎ የቀረቡ ቃላትን በምዕላድ ነጣጥላችሁ አሳዩ።**

| ተ.ቁ | ቃላት | ምዕላዶች |
|---|---|---|
| 1 | ምሳሌ፡ እንደተናገሩት | እንደ-ተናገር-ኡ-ት |
| 2 | በመንከባከባቸው | |
| 3 | እንደለበሳችሁ | |
| 4 | ቤተመንግሥታችን | |
| 6 | በወንበራቸው | |
| 7 | ልብሶቻችንን | |
| 8 | ቤቱን | |
| 9 | ሀገራችንን | |
| 10 | ትውልዱን | |

**ክፍለጊዜ አስራአራት**

**ለ. እናንተ ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ አስር ቃላትን ፈልጋችሁ በምዕላድ ከፋፍሉ።**

**ክፍለጊዜ አስራአምስት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ስለቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎች ልዩነት ትማራላችሁ። ስለሆነም የተሰጣችሁን ማስታወሻና ምሳሌዎች መነሻ በማድረግ መልመጃዎቹን በትዕዛዛቸው መሠረት ሥሯቸው።

**ማስታወሻ**

ተሳቢዎች በግሱ የተገለጸው ድርጊት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚያርፍባቸው ናቸው። በዚህም መሠረት ተሳቢዎች ቀጥተኛ እና

ኢ-ቀጥተኛ በመባል ይታወቃሉ።

ለምሳሌ “እሷ ለወንድሟደብዳቤጻፈች።” በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ ግሱ “ጻፈች” ሲሆን በግሱ የተገለጸው ድርጊት በቀጥታ ያረፈው “ደብዳቤ” በሚል ስም ላይ ነው። ስለሆነም “ደብዳቤ” ቀጥተኛ ተሳቢ ሲሆን “ለወንድሟ” የሚለው ደግሞ ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ነው።

## ክፍለጊዜ አስራስድስት

### መልመጃ አራት

ሀ. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን ለይታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ፡ ልጁ በእርሳስ ሥዕል ሳለ። በእርሳስ የሚለው ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ሲሆን ስዕል ደግሞ ቀጥተኛ ነው።

1. እሱ መጽሓፉን ቀደደ።
2. ሰውዬው በዱላ ውሻውን መታው።
3. መጽሓፍ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ።
4. እሷ መስኮቱን ከፈተች።
5. እሷ በመኪና ሄደች።
6. ናሲሴ ለልጇ ልብስ ገዛች።

## ክፍለጊዜ አስራሰባት

ለ. ቀጥተኛ ተሳቢዎችን በመጠቀም የራሳችሁን አምስት ዓረፍተነገሮች መሥርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራስምንት

ሐ. ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን በመጠቀም የራሳችሁን አምስት ዓረፍተነገሮችመሥርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## ሙዳየቃላት

መረዳት (Comprehension)፡- የንግግርን ወይም የጽሑፍን ቋንቋ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ሂደት፣

መነጠል (Segmenting)፡- አንድን ሙሉ ቃል በቀለም ወይም በምዕላድ የመነጣጠል ሂደት

መገመት (prediction)፡- ከማንበብ/ከማዳመጥ በፊት ወይም በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት ቀጥሎ ምን ሊመጣ ወይም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፤

ማጣመር (blending)፡- በቀለሞች ወይም በምዕላዶች ተነጣጥሎ የቀረበን ቃል በአንድ ላይ አጣምሮ የመናገር፣ የማንበብ ወይም የመጻፍ ሂደት፣

ቃላት በደቂቃ (ቃበደ) (WPM)፡- በአንድ ደቂቃ በፍጥነት የተነበቡ ቃላት ብዛት፣ በአንድ ደቂቃ በትክክል የተነበቡ ቃላት ብዛት (WCPM ቃላት ትክክል በደቂቃ (ቃትበደ))፣ (የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ደረጃ ለመወሰን ያገለግላል።)

ቅጥያ (Affix)፡- በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚቀጠሉ ትርጉም አዘል ቅጥያዎች፣ (በቃል መጀመሪያ ሲቀጠሉ ቅድመአምድ ቅጥያ (Prefix)፣ በቃል መጨረሻ ሲቀጠሉ ድህረአምድ ቅጥያ (Suffix) ይባላሉ።)

የቢጋር ሠንጠረዥ (Graphic organizer)፡- የሀሳብን ግንኙነት በሥዕል ወይም በግራፍ ወይም በሠንጠረዥ የማደራጀ ስልት፣

በትብብር መማር (Cooperative learning)፡- አንድን የትምህርት ይዘት በጋራ እየተረዳዱ የመማር ሂደት፣

ተራኪ ጽሑፍ (Narrative text)፡- ታሪክን በጊዜ ወይም በቦታ ወይም በድርጊት ቅደምተከተል የሚያሳይ የጽሑፍ መዋቅር

ትክክለኛነት (Accuracy)፡- አንድን ቃል፣ ሐረግ ወይም ዓረፍተነገር ያለስህተት የማንበብ ችሎታ፣

ድብኝት፡- ከጭቃ የተሠራ የእህል ማስቀመጫ፣ ጎተራ

ጉራማይሌ፡- የተለያዩ ቋንቋዎችን በመደባለቅ የሚቀርብ ድብልቅ ንግግር ወይም ጽሑፍ

ጦስ፡ ምክንያት፤ ሰበብ

አስረጂ ጽሑፍ (Expository text)፡- መረጃ ሰጪ የሆነ ጽሑፍ ሆኖ ስለአንድ ርዕሰጉዳይ ወይም እውነት ለማስተማር/ ለማስረዳት የሚያገለግል ጽሑፍ፣

ፀዳል፡- ብርሃን ወይም የብርሃን ፍንጣቂ

አረጋዊ፡- አዛውንት፣ በዕድሜ የገፋ

አረንቋ፡- ረግረግ፣ ማጥ

አቀላጥፎ ማንበብ (Fluency)፡- ፊደላትን፣ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጭ በሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ፣

አንብቦ መረዳት (Reading comprehension)፡- አንድ ጽሑፍ አንብቦ ትርጉም የማግኘት ችሎታ፣

**አዳምጦ መረዳት** (Listening comprehension)፡- ንግግርን ወይም የሚነበብ ጽሑፍን አዳምጦ ተረድቶ ትርጉም የመስጠት ችሎታ፣

**ዐቢይ/ዋና ሀሳብ** (Main idea)፡- ከምንባብ ተጨምቆ የሚወጣ አንኳር መልዕክት፣

**ዐውድ** (Context)፡- ለአንድ እንግዳ ቃል ፍቺ ፍንጭ የሚሰጡ ከቃሉ በፊት ወይም በኋላ የሚገኙ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ዓረፍተነገሮች፣